# Studies on Contemporary Ethiopian Social Issues

Ghelawedwos Araia, PhD
**Institute of Development and Education for Africa (IDEA)**

December 1, 2014
**Dedicated to Hanna Lalango** **ለ ሃና ላላንጎ መታሰቢያ**

This scholarly article on Ethiopian social issues attempts to fill a lacuna in Ethiopian contemporary social studies with particular focus on social ills that have proliferated in Ethiopia as of recent but ironically underreported by the Ethiopian media. Social problems, including crimes, are not unique to Ethiopia and they are apt to develop, if not mushroom, especially in nascent expanding urban centers. However, we Ethiopians, and especially intellectuals, have historical responsibility to research and study the social problems and influence public policy for the sole purpose of overcoming the problems.

Disciplines like sociology and social studies should not be limited to studying the larger society in the context of 'social relationships' and/or 'the functioning of societies'; they should transcend the traditional approaches and focus rather on 'problem solving' and 'decision-making' by way of empowering citizens and consequently by enabling them to acquire necessary skills and deal with critical social issues.

The publication of this study is inspired by the tragic death of the fifteen-year old young Ethiopian girl by the name Hanna Lalango, who was abducted by criminals, stabbed and gang raped, and died of her injury caused by her abductors. Before she died, however, her father Ato Lalango Ayese witnessed the last gasp of his daughter before she made the transition in the hospital. Despite the agony and sorrow they encountered, however, the family of Ato Lalango, including his wife Weizero Tirfe Woldesenbet, and his daughter Martha Lalango, bravely came out to a public forum and discussed the life and death of their last child, but most importantly they have conveyed a message of historic proportions that could serve as a lesson to all Ethiopians, and perhaps by default redeem the social ills that could very well undermine the social fabric of Ethiopia unless it is checked before it is too late. The message of the Lalango family is pure and simple: Ethiopians must collectively guard their respective neighborhoods by being vigilant against criminals and by acting as community militias. (The information on the tragedy of Hanna was obtained from the Addis Ababa Police Report video clip of November 30, 2014).

In anticipation to the tragedy that happened to the Lalango family (and other countless families across the board in Ethiopia), I had prepared a lengthy study (in Amharic) on the social dimension of the Ethiopian society in 2013 for a group of Ethiopians in North America. I have now decided to release the study for public consumption (Ethiopians and non Ethiopians alike) so that they can better understand Ethiopia's social problems and come up with solutions.

# የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ገጽታ ጥናታዊ ጽሑፍ

ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር

የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ)

ኒው ዮርክ ዩናይትድ ስተይትስ

November 2013

All Rights Reserved. Copyright © Ghelawdewos Araia 2013

## ማውጫ

I. የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ደኅንነት ጥናታዊ ጽሑፎች

ሀ. ፍችና የቤተሰብ መፍረስ

ለ. የቤት ሁከት

ሐ. የሴቶች ምጣኔ-ሃብታዊ ፍች በከተማ

መ. የኮረዳዎች እርግዝና ማሕበራዊ ችግር

ሠ. እናታዊ ሞት በኢትዮጵያ

ረ. የወጣት ስራ አጥነት ችግር በአዲስ አበባ

ሰ. ጫት ቃሚ ወጣት በኢትዮጵያ

II. የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት በኢትዮጵያ፡ ምሳሌዎችና ፍጆታ ዋጋዎች

III. እርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ በኢትየጵያ

IV. እርጅና እና ድህነት በኢትዮጵያ

V. ማሕበራዊ ችግሮችና ሕብረተ-ሱታፌ ስትራተጂ

VI. የኢትዮጵያ ስደተኞች ማሕበረሰብ

VII. አዳዲስ የፈለቁ ማሕበራዊ ገጽታዎች

VIII. ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተጸነሰው ከፖለቲካና ምጣኔሃብታዊ ትንታኔዎች ባሻገር የኢትዮጵያ ማህበራዊ ገጽታ ለማካተትና ከሞላ ጎደል ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ማህበራዊ ችግሮችን በቅጡ ለማጥናት፣ የኋላ ኋላ ደግሞ ለተማሪዎች፣ ለመምህራን እንዲሁም ባገር ደረጃ ኢትዮጵያን ለሚመሯት ባለሥልጣናት መምርያና ፖሊሲ ማውጫ ይሆናል ከሚል እምነትና ግምት ነው።

የአንድ ሕብረተሰብ ማሕበራዊ ጉዳዮች ከፖለቲካዊ ምጣኔሃብታዊና ስነልበናዊ ዘርፎች ተነጥሎ የሚታይ አይደለም፣ እጅግ ውስብስብ ባለ መንገድ የተቈራኙ ናቸውና። ሆኖም ግን የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ትኵረት በኢትዮጵያ ማሕበራዊ ገጽታ ላይ ስለሆነ ማሕበራዊ ጉዳዮችን በዝርዝር ለማቅረብና ለመተንተን ተመኵሯል።

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በመሠረቱ በማሕበራዊ ስነ-ሓሳብ ላይ በመመርኮዝ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ማሕበራዊ ገጽታን ይወያያል፣ በጽሑፉ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ የመወያያ ዓበይት ነጥቦችና ርእሰ-ነገሮች ደግሞ በልዩ ልዩ መረጃዎች፡ ጥናትና ሰታቲስቲክስ በመደገፍ ግዙፉን የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ጉዳዮችን አመርቂ በሆነ መንገድ ለማተትና በተቻለ መጠንም መፍትሔዎችን በመጠቆም ለማገናዘብ ጥረት ተደርጓል።

እንዲህ ያሉ ጥናታዊ ጽሑፎች በምናቀርብበት ጊዜ ግን መጀመርያ ማድረግ ያለብን ሰፊና ጠለቅ ያለ ማሕበራዊ ስነሐሳብ እንደ መሳርያ መጠቀም ነው። ሰነ-ሐሳቡ ሕብረተሰቡን ለመመርመርና ማሕበራዊ ጉዳዮችን በቅጡ ለመረዳት ያስችለናል፣ ያለ ስነ-ሐሳብ የማንኛውም ሕብረተሰብ ማሕበራዊ ገጽታን በጥልቀት ተመራምረን ማጤን አንችልም። ስለሆነም በዚሁ አጋጣሚ ታዋቂ የሆኑትን የባህላዊ፡ ሕብረተሰባዊና ማሕበራዊ ስነ-ሓሳቦችን በሚመለከት ዘዴዎች ያራመዱና ያጐለመሱ ቀዳሚ ተማራማሪዎችና ሊቃውንት ማስተዋወቁ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

የመጀመርያው ተመራማሪና 'ሰነ-ሕብረተሰብ' (sociology) የሚል ጽንሰ-ሐሳብ ያቀረበው ኦገስት ኮምት (1794-1859) የሚባል ፈረንሳዊ ነው:: ለነገሩ ስነ-ሕብረተሰብ የሚል ቃል ወይም ሐሳብ ከ ኮምት በፊትም ይዘወተር ነበር፣ ግን ሃሳቡን በሚያረካ መንገድ የገለጸው እሱ ስለሆነ የሐሳቡን አመንጪ እንደሆነ በትምህርትና ቤተ-ምርምር ተቋማት ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል። በኮምት የቀረቡ ሁለት ዓበይት ነጥቦች 'ማሕበራዊ ቋሚነት' (social static) እና 'ማሕበራዊ ግስጋሴነት' (social dynamic) ሲሆኑ የመጀመርያው አንጻራዊ በሆነ መንገድ ሕብረተሰቡ ባለበት ጸንቶና ተረጋግቶ የሚቀጥል ሲሆን ሁለተኛው ግን ማንኛውም ሕብረተሰብ በለውጥ የሚቀየር ነው የሚል ነው።

ከኮምት በኋላ ታላቁ የስነ-ሕብረተሰብ ተመራማሪ ኤሚል ዱርካይም (1858-1917) ሆኖ የስነ-ሕብረተሰብ የትምህርት ዓይነት የፈጠረ፣ እንድያውም የስነ-ሕብረተሰብ ወይም ሶስዮሎጂ አባት መሆኑን ነው የሚነገርለት ፈረንሳዊ ሊቅ ነው። ዱርካይም "ስነ-ሕብረተሰብ ስለ ግለሰብ ተግባር የሚገፋፉ ሐሳቦች ሳይሆን

ስለ ሕብረተሰብና ስለ ባህል ነው" ይላል። ዱርካይም፡ ታሪክም ሳይቀር ያንድ ማሕበራዊ ስርዓት የለውጥ ሂደት ነው ብሎ ይከራከራል፣ ሳይንስም ሳይቀር ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለማጥናት ተደጋጋሚ ምሳሌዎችን (patterns) ማጥናት ይኖርበታል ብሎ ያምን ስለነበር ከዚሁ አመለካከትና ግንዘቤ በመነሳት ደግሞ ስታቲስቲክስ የተባለውን ትምህርታዊ መመዘኛ መሣርያ የመጀመርያ ፈጣሪ ሆነ። እንደ ዱርካይም አባባል "ስታቲስቲክስ መደበኛ ተደጋጋሚ ምሳሌዎች የአንድን ማሕበራዊ መዋቅር የአስገዳጅ ኃይሎች መሠረት መሆናቸውን ያሳየናል" ይላል። በተጨማሪ፡ ዱርካይም 'ደረጃ/ተመን' የአንድን ሕብረተሰብ ወይም ማሕበረሰብ ሁኔታ አመልካች ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ሕብረተሰቦችን የሚንጸባረቁ ወጎችና እምነቶች አንጻራዊ በሆነ መንገድ እንድናጠና ይረዳናል ይላል።

ከነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ስነ-ሐሳቦች መንደርደርያ በማድረግ ታድያ ዱርካይም የአንድን ሕብረተሰብ ማሕበራዊ አንድነትን፡ ሕግጋትን፡ የኃይማኖት እምነቶችን፡ እንዲሁም ራስን የመግደል ዝንባሌዎችን በሰፊው ማጥናት ጀመረ። ከነዚሁ ጥናትና ምርምር በመነሳትም በ1893 ዓ.ም. የመጀመርያው <u>የሕብረተሰብ የስራ ክፍፍል</u> የተሰኘውን መጽሓፉን አበረከተ።

በዱርካይም አመለካከት፡ <u>ራስን መግደል</u> በሚል ርእስ የጻፈውን ሌላ መጽሐፍ ውስጥ የኢምቢታ ጸባይ ማሕበራዊ እውነታና የሕብረተሰቦች ጸባይ እንጂ የግለሰቦች አይደለም በማለት ካሰቀመጠው በኋላ የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ማሕበረሰቦችና የላላ ግንኙነት ያላቸው ማሕበረሰቦችን አወዳደረና ከማሕበራዊ መዋቅር ተነጥለው በግላዊ ኑሮ የሚኖሩትን የፕሮተስታንት ኃይማኖት ተከታዮች በይበልጥ ራስን የመግደል ዝንባሌዎችን እንደሚያሳዩ ተገነዘበ። የወንጀሉም መንስኤ በተመሳሳይ መልክ ያስቀምጠዋል። በመጨረሻም ዱርካይም የሚከተሉትን ዓበይት ጥያቄዎችን ያቀርባል፦ ሕብረተሰቦች ኅብረ-ባህል ወይም ኅብረ-ብሔር ሆኖው የጠነከረ አንድነትን መጐናጸፍ ይችላሉ ወይ? ግለሰቦች ከወግ አጥባቂ የግብረገብ ድንጋጌዎችን ነጻ ወጥተው በሕብረተሰባቸው ውስጥ ሐላፊነትን መሸከም ይችላሉ ወይ? ቆየት ብለን እነዚህን ጥያቄዎች አሁን ካለው የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ገጽታ ጋር በማገናዘብ እንመልሳቸዋለን።

ከዱርካይም በኋላ ታዋቂ የሕብረተሰብ ተመራማሪ ማክስ ቪበር (1864-1920) የተባለውን የጀርመን ምሁርና ተመራማሪ ነው። ቪበር እንደ ዱርካይም ሳይሆን ሕብረተሰብን ያየው ከተግባር አገባብ አንጻር ነው፣ ተግባሩም ከትርጉም እቅድ ካለው ጸባይ ጋር የተቆራኘ ነው ይላል። ባጭሩ ቪበር የተከተለውን የጥናት ምሳሌ እንደ ዱርካይም ስታቲስቲክስ እና በተግበር የተፈተነ (empirical) ሐቅ - የኋላኛውን በመጠኑ በመቀበል - ብቻ ሳይሆን 'አንጻራዊ የታሪክ ዘዴ' በመከተልም ጭምር ነው። የቪበር ዘዴ ዋና ጥቅሙ ሕብረተሰብን ባጠቃላይ፣ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ደግሞ በተለይ ለማጥናት ከተፈለገ ልዩ ልዩ የሕብረተሰቡ አካላት (ተቋማት፡ ልምዶች፡ ኃይማኖቶች ወዘተ) አንጻራዊ በሆነ መንገድ ማጥናት ይበጃል የሚል አመለካከት ስላለው ነው። ለምሳሌ "የአብዮቶች ባህርይ እንድንረዳ ከተፈለገ የመደብ አሰላለፎችን ማወቅ አስፈላጊ ነው፣ በይበልጥ አስፈላጊ የሚሆነው ደግሞ የፖለቲካ ተግባር ነው" ይላል ቪበር። በዚሁ

አመለካከቱ ቬበር ወደ ካርል ማርክስ እጅግ በጣም ይቀርባል። ለዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ግን የአብዮት ባህርይ ሳይሆን የመደብና ማሕበራዊ ጉዳዮችን እንዴት እንደሚያያዙ ሊረዳን ይችላል።

አንቶንዮ ግራምሺ (1891-1937) ጣልያናዊ ተመራማሪና ማርክሲስት ደግሞ ለዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ጠቃሚ ስነ-ሐሳቦችን ያበረክትልናል። የግራምሺ ምሁራዊ ጽሑፎች 'ሽጂመኒ (hegemony) የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ሆኖ ቀጥተኛ ትርጉሙ ደግሞ በአንድ ያገዛዝ ስልት ውስጥ ተገዢው ክፍል ለባለሥልጣኑ እንዲገዛ ፈቀደኛ ሆኖ ሲገኝ ማለት ነው፣ በኃይል ሳይሆን በተጽእኖ። የግራምሺ አመለካከት ለዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ብዙ ጠቄሜታ አለው፡ ምክንያቱም የሴቶችና የወንዶች ግንኙነትን አስመልክቶ፡ እርግዝና፡ ፍች፡ የፍርድ አሰጣጥ (ፍትሕ)፡ የቤት ሁከት ወዘተ ከ'ሽጂሞኒ ውጭ መግለጽና መተንተን አንችልም። 'ሽጂሞኒ ባማርኛ ቀጥተኛ ትርጉም ስለሌለው በዚሁ ጽሑፍ 'ተጽእኖዊ-አገዛዝ' የሚል ሐረግ ተጠቅምያለሁ።

ሌላው ለዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ የምንጠቀምበት ተመራማሪ ምሁር ዝነኛው የአመሪካ የስነ-ሕብረተሰብ ሊቅ ሲ ራይት ሚልስ (1916-1962) ነው። ሚልስ በ1950ዎቹ በኮሎምብያ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ሕብረተሰብ ፕሮፌሰር ነበር። መጀመርያ የታወቀውና ዝናኛ የሆነው ደግሞ "ረቂቅ ግብረፈተና (abstract emprícism) ስታቲስቲክስ እና የአሰሳ ጥናት ዘዴ (survey methods) የብዙ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ገጽታዎች ይደብቃሉ እንጂ በቅጡ አይገልጹም" ብሎ ከተከራከረ በኋላ ነው።

ሚልስ ከፍተኛ ዝናን ያተረፈው ግን በደረሳቸው ሦስት መጻሕፍት ነው። ርእሶችም የሚከተሉት ናቸው፦ 1) White Collar (1951)፣ The Power Elite (1956)፣ እና The Sociological Imagination (1959)። የመጀመርያው መጽሓፉ በአማሪካ በተከሰተው ግዙፍ ማእካላዊ መደብ፡ የተክኒክ ምሁራን፡ ሊሂቃን፡ የቢሮ ሰራተኞችና ዝቅተኛ ስራ አስክያጆችን በሚመለከት ነበር ያተኮረው። በሁለተኛው መጽሓፉ አመሪካን የሚገዙ ሦስት ዓይነት ሊሂቃንን ይገልጻል፦ የትላልቅ ኮርፐረሽኖች ሥራ አስክያጆች፣ የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ ደረጃ የሥራ አስክያጅ ዘርፍ፣ እና የወታደራዊ-ኢንዱስትሪ ወሳኝ ክፍል። ሦስተኛው መጽሐፉ በምሁራንና ዩኒቨሪሲቲ ፕሮፌሰሮች ላይ ያተኮረ ሆኖ ምን ዓይነት ሚና መጫወት እንዳለባቻው ደግሞ በዚህ ዓይነት ያስቀምጠዋል፦ "የስነ-ሕብረተስብ ተመራማሪ የሕዝብ ምሁር መሆን አለበት፣ ከፖለቲካ ሥራዎች ጋር በአመርቂ ችሎታዎች መቆራኘት አለበት፣ የስነ-ሕብረተሰብ ምሁር፡ ለነገር ይቅደም፡ የሕብረተሰቡ ዜጋ መሆን አለበት" ይላል። ሕብረተሰባዊ ራእይ ፕሮፌሶረች ግዙፍን የታሪክ አውድማ እንድያዩና የግለሰቦችን የውስጥ ሕይወትና የውጭ ሥራዎቻቸውን በቅጡ እንዲመለከቱ ይረዳቸዋል። እንግዲህ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ለማጥናት ከተፈለገ ሲ ራይት ሚልስ ያነሳቸውን ዓበይት ሕብረተሰብ-ነክ ጥያቄዎችን ማገናዘብ አስፈላጊ ይሆናል።

ከላይ የተጠቀሱትን ምሁራዊ ስነ-ሐሳቦችን ከኢትዮጵያ ተጨባጭና ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ከማሕበራዊ ጉዳዮችን ጋር ያላቸውን

አግባብነት በማነጻጸር እናቀርባቸዋለን። የመጀመርያው ርእሰ-ነገር ማለትም ፍችን አስመልክቶ በዚሁ ጽሑፍ የቀረቡት አበዛኞቹ የመወያያ ነጥቦችን በአዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ የማሕበራዊ ደኅንነት ክፍለ-ትምህርት የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ባቀረቧቸው ጥናቶች ላይ በመንተራስ ነው። በዚሁም በአንደኛው ክፍል ሁሉም ንዑስ ርእሰ-ነገሮች ከዓብዩ የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ደኅንነት ርእሰ-ነገር ጋር እንወያይባቸዋለን።

## I. የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ደኅንነት ጥናታዊ ጽሑፎች

### ሀ. ፍችና የቤተሰብ መፍረስ

በዚሁ ንዑስ ርእሰ-ነገር የፍች መንስኤና በቤተሰብ ላይ የሚያደርገውን ጫና እናያለን። በፍች ጫና የደረሰባቸው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ አባላት አብዛኞቹ የቤት እመቤቶች ናቸው። የተፈቱ ሴቶች የምጣኔ ሃብታዊ ድክመት ስለሚታይባቸው ለመኖር ያህል እጅግ ዝቅተኛ እና መደበኛ ባልሆነ የምጣኔሃብት ዘርፍ ውስጥ በመሰማራት፡ በቤት የተሰሩ ነገሮችን በመሸጥ፣ እንጨት በመሰብሰብና ለገበያ በማቅረብ ወዘተ ኑሮአቸውን ለመግፋት ይጥራሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ በሕብረተሰብ ዘንድ ፍች ተቀባይነት ስለሌው የተፈቱ/የተፋቱ ሴቶች ማሕበራዊ ጫና ይደረግባቸዋል።

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ‘የወጣት ፍትሕ ውጥን ጽሕፈት ቤት’ በተሰኘው መጽሔት በ2007 ዓ.ም. “ፍትሕና ሕጻን” በሚል ርእስ ሐተታ አቅርቦ ነበር። በሕጻናቱ ላይ ከፍተኛ የቅርብና የሩቅ የስነልቦናዊ ቀውስ ሊያደርስ ይችላል ይላል። ቀደም ብሎ በተደረገው ጥናት ደግሞ የሥራና የማሕበራዊ ጉዳዮች አካል በ1996 ዓ.ም. በዚሁ መልክ ያስቀምጠዋል፦ “ብዙ ቤተሰቦች በድህነት ምክንያቶች ወደ ፍች እንደሚሰማሩና እንደሚበታተኑ፣ የዚሁ ውጤት ደግሞ በየከተሞቹ የተነፈጉ ህፃናት መብዛት ሆኗል”።

ጀልሰንና ላርሰን የተባሉ ምሁራን ባቀረቡት ዘገባ “45 ከመቶ የመጀመርያ ጋብቻ በኢትዮጵያ በሰላሳ ዓመታት ውስጥ ወደ ፍች ያመራሉ” ይላሉ። በ1994 ዓ.ም. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በአዲስ አበባ እንዳመለከተው ከሆነ ከ1,722,391 ግለሰቦች 506,852 ጋብቻቸውን ሲቀጥሉ፣ 97,147 ደግሞ በፍች ተለያይተዋል። በተጨማሪ የሥራና ማሕበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር በ1996 ባቀረበው ዘገባ 60 ከመቶ የኢትዮጵያ ቤተሰቦች አስከፊ በሆነ ድህነት ውስጥ እንደሚገኙና ይኸም ለፍች አንዱ ምክንያት መሆኑን ዘግቦታል። ፍችና የቤተሰብ መፍረስን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ የማሕበራዊ ደህንነት ክፍለ-ትምህርት በሰርክአለም የቀረበ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ አለ።

### ለ. የቤት ሁከት

የቤት ሁከት ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች ዘንድ አካላዊ ኃይልን በመጠቀም አንዱን የቤተሰብ አባል ማጥቃት ማለት እንደሆነ ነው የሚገለጸው። ሁከት ግን ከድብደባ እስከ ስነ-ልቦናዊ ጥቃት ብሎም እስከ ግድያ የሚያደርስ

ማሕበራዊ ችግር ነው። የዚሁ ማሕበራዊ ችግር በርካቶቹ ሰለባዎች ደግሞ ሴቶች ስለሆኑ፣ በሴቶች ላይ የሚደረገው ሁከታዊ ጥቃት እንዲጠፋ የተባበሩት መንግሥታት አዋጅ አውጥቶ ነበር። ለዚሁ ጥናት አስተዋጽኦ ያደረገች የአዲስ አበባ የኑቨርሲቲ የማሕበራዊ ደኅንነት የድህረ-ምረቃ ተማሪ የሆነችው የኔነሽ ታደሰ ነች። የኔነሽ ባደረገችው ጥናት በደቡብ መሃል ኢትዮጵያ በመስካን እና መረቆ ወረዳዎች 59 ከመቶ ሴቶች የግብረስጋ ሁከት እንደሚደርስባቸው፣ 49 ከመቶ ደግሞ በሆነ ጊዜ የአካል ሁከት እንደሚደርስባቸው ገልጸዋለች። ከጥናቱ አስራ ሁለት ወራት አስቀድሞ 44 ከመቶ ሴቶች በግብረስጋዊ ሁከት፣ 29 ከመቶ ደግሞ በአካላዊ ሁከት እንደሚጠቁ ተደርሶበት ነበር። ሌላው የዚሁ ጥናት ደጋፊ ደግሞ የዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት ያቀረበውን ዘገባ (2005 ዓ.ም.) ሆኖ ደርጅቱ ባደረገው ቃለ መጠይቅ 59 ከመቶ ሴቶች ከቅርብ ሽርኮቻቸው የግብረስጋ ጥቃት እንደሚደርስባቸውና 29 ከመቶ ደግሞ የአካል ሁከት እንደሚደርስባቸው ለማረጋገጥ ተችሏል። የዚሁ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥናት ደግሞ እውነትነት እንዳለው የኢትዮጵያ ሴቶች ጠበቆች ማሕበር አረጋግጦታል።

በሰኔ 2007 ዓ.ም. በአዲስ አበባ 'የቤተሰብ ጉባኤ፡ ሚስጢሩን እናውጣ' በሚል ርእስ ስብሰባ ተከሂዶ ነበር። ጉባኤው በ2002 የተጀመረውን የሴቶች ጉባኤ ተቀጥያ ስድስተኛው ስብሰባ ሆኖ ዓላማው ደግሞ የሁከት መንስኤዎችን ለቤት ሁከት ማሕበራዊ ችግር ጠንቅ መሆኑን ለማሳየት ነበር። ነገር ግን የቤት ሁከትን አስመልክቶ የተለያዩ አመለካከቶችና ዘገባዎች ነው የሚቀርቡት። ስለሆነም በዚሁ መጠን ልዩ ልዩ ተቋማት፡ ሕግጋትና ሴቶችን በሚመለከት ሚኒሰትሪ ሳይቀር ተፈጥሯል። እነኚ ተቋማት ደግሞ ከሞላ ጎደል 'ሃገራዊ የሴቶች ጉዳይና የጾታ እኩልነት' መሠረትን በማድረግ መጠነ-ሰፊ ውይይቶችን አካሂደዋል።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ደግሞ የሴቶችን መብት በሚመለከት ብዙ አንቀጾችን አካቷል። ለምሳሌ አንቀጽ 35 በጠቅላላ ስለ ሴቶች መብት ነው። በተከለሰው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ፣ ማለትም ቁ. 414/2004 ደግሞ የቤት ሁከት ልዩ ስፍራ ይዟል፣ የዚሁ ወንጀለኛ መቅጫ አንቀጽ 564 በማንኛውም የጋብቻ ግንኙነት ላይ ሁከትን የሚያደርስ የውሕደቱ አባል በሕግ ተጠያቂ እንደሚሆን ይገልጻል። የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ 2000 እንዳመለከተው ደግሞ ባልና ሚስት በሕጉ ፊት እኩል መብት እንዳላቸውና ጋብቻቸው ሕጋዊነት የሚኖሮው ደግሞ ሁለቱ የጋብቻ አባላት ለጋብቻው ነጻና ሙሉ ድጋፍ ሲያደርጉ ነው ይላል።

የሴቶችን መብት ለማረጋገጥ በማለት ደግሞ 'የሴት ጉዳይ ሚኒስትሪ' ተቋቁሟል። የሚንሰትሪው ዘርፎች በክልሎችና በሌሎች ሚኒሰትሮች እንዲዋቀሩም ተደርጓል። አጠቃላይ የሴቶችን ጉዳይ አወቃቀር በፌደራል፡ በክልል፡ በወረዳና በቀበሌ ከሞላ ጎደል ሲተገበር የኢትዮጵያ የሴቶች ጉዳይ ማሕበር ደግሞ ተቋቁሟል።

ከላይ ከጠቅስናቸው የሴቶች ማሕበራዊ ችግሮች በተጨማሪ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማሕበራዊ ደህንነት ድሕረ-ምረቃ ተማሪ የሆነችው እመቤት ወልደየስ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርባለች። ባደረገችውም ጥናት ላይ የሴቶች መብት በሽርኮቻቸው እንዴት እንደሚጣስ ካሰመረችበት በኋላ ከ1995 ዓ.ም. እስከ 2001 ዓ.ም. ለ 28 የአዲስ አበባ ፖሊስ ጣብያዎች የቀረቡት ልዩ ልዩ ወንጀሎች እንደሚከተለው

አቅርበዋለች፦

| | ሴቶችን መድፈር | ድብደባ | ጠለፋ | የግድያ ሙከራ |
|---|---|---|---|---|
| 1995 | 217 | 772 | 8 | 40 |
| 2001 | 378 | 6401 | 46 | 47 |

የሁለቱ ዓመታትና ከመሃሉ ያሉትን ዓመታትን በግምት ከገባ ደግሞ የወንጀሎቹ ጠቅላላ ድምር፦

| | ሴቶችን መድፈር | ድብደባ | ጠለፋ | የግድያ ሙከራ |
|---|---|---|---|---|
| | 1995 | 21,987 | 194 | 280 |

የወንጀሎቹ አጠቃላይ አዝማምያ ከተመለከትን ወንጀሎች እየበዙ መሄዳቸውን ነው የሚያሳየን። ወንጀሎችን ጠለቅ ባለ መንገድ ማጥናት ከፈለግን ደግሞ ቀደም ብለን የጠቀስነውን የዱርካይም 'የድግግሞሽ ምሳሌ' (pattern) አርአያነት ሊጠቅመን ይችላል። በወንጀለኛው ብቻ ላይ ማትኰር ሳይሆን ባጠቃለይ የወንጀሎች ምንጭ ከግዝፉ ማሕበረሰብ በምን ረገድ እንደሚተሳሰሩ ማጥናት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በከተሞች የስርቆት ወንጀል ከበዛ ምናልባት መንስኤው ስራ አጥነት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ወንጀሎች ከበዙ ወይ ሕብረተሰቡ በጠና ታሟል ወይም ደግሞ በከፊል መፍትሔ ያልተገኙባቸው ማሕበራዊ ችግሮች አሉ ማለት ነው።

የኢትዮጵያ የሴቶች ጠበቆች ማሕበር በ2008 ዓ.ም. በ208 አዋቂ ሴቶችና 97 ተማሪ ሴቶች ባደረገው ጥናት ላይ አብዛኞቹ ሴቶች ሁከትን በሚመለከት መግለጫ አይሰጡም። ሌላው በሴቶች ላይ የሚደርሰው በደል በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች ዘንድ የሚተገበር ተመሳሳይ ሁከት ሆኖ በጋምቤላ፥ በኦሮምያ እና በአፋር ክልሎች ግን የላቀ የሴት ድብደባ እንደሚካሄድ ተደርሶበታል።

የሴቶች የበታችነትና ጭቁንነት ከወንድ የበላይነት ርእዮተዓለም የመነጨ ቢሆንም ይኸን አድማሳዊ ባህርይ ያለው ርእዮተዓለም በአዙር መንገድ በሴቶች ስነልቦናዊ አመለካከት ጫና ስላደረሰ፣ የድብደባ ሰላባ የሆኑትን ሴቶች ሁከትን እንደ ወንጀል አይቆጥሩትም። በጽንፈኛ መልኩ ደግሞ 'ቅናትና ሁከት' የአንድ ወንድ/ባል ለትዳር ወይም ቃል ኪዳን ያለው ዝግጁነት ያሳያል ብሎው የሚያምኑ ሴቶች አሉ። ስለሆነም በርካታ ሴቶች የድብደባ ዓይነት ሁከት በዝምታ ከማፈን በስተቀር በይፋ ለመናገር ፍላጎት የላቸውም። ርእዮተዓለሙና የሴቶች ተቀባይነት ወይም ተምበርካኪነት ቅድም የጠቀስነውን የግራምሺ 'ተጽእኖዊ-አገዛዝን' ስነ-ሐሳብ የሚያንጸባርቅ ነው።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 "ማንኛውም ሰው ከአካላዊ ጉዳት መከላከል ወይም ጥበቃ መብት አለው" ይላል። የወንጀለኛ መቅጫ አንቀጾች 531-544 ደግሞ "ለሌላ ሰው አካላዊ ጉዳት ምክንያት ወይም የሰውን ጤና የሚያኮላሽ ከሆነ

ወንጀለኛው በዚሁ ሕግ ይጠየቃል" ይላል። ቀጥሎም "ሴቶች ከባሎቻቸው፣ የወንድ ጓደኞቻቸው ወይም ከማንኛውም ሰው ይጠበቃሉ" ይላል። ነገር ግን ሕግጋቱ በወረቀት ይስፈሩ እንጂ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያት ጋር በተያያዘ የሴት ድብደባ ወንጀል በጣም አነስተኛ በሆነ መልኩ ነው የሚዘገበው።

ወንጀለኛው መቅጫ በተጨማሪ በሕዝብ ዘንድና በግል ደረጃ ለሚተገበሩ ጸረ-ሴት ሁከቶች ለያይቶ ያስቀምጣቸዋል። ሕጉ ከቤት ውጪ ለሚተገበሩ ጸረ-ሴት ሁከቶችን በይበልጥ ሚዛን የሰጠው ይመስላል። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ሴቶች የአካልና ስነልቦናዊ ሁከት ሰለባ የሚሆኑት በቤት ውስጥ ስለሆነ ሕጉ በዚህ ረገድ ላይ ድክመት አሳይቷል።

### ሐ. የሴቶች ምጣኔሃብታዊ ፍች በከተማ

ሰምሃል ጌታቸው የፍች ምጣኔሃብታዊ ገጽታውና በከተሜ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጫና ጥናት አድርጋለች። ባደረገችውም ጥናት መሠረት 87 ከመቶ ሴቶች የልጆች ጠባቂዎች ቢሆኑም ቅሉ ለልጅ እርዳታ የሚደረግላቸውን 50 ከመቶዎቹ ነው። ብዙውን ጊዜ ለአንድ ልጅ ከመቶ ብር በታች ነው የሚሰጠው፣ ይኸም ቢሆን ቀጣይነት ያለው ክፍያ አይደለም። ይኸው ችግር በልጆች ላይ ጫና ስለሳደረ ትምህርታቸውን አቋርጠው እንደሚወጡ የትምህርት ሚኒስተር በ2004 ዓ.ም. ባደረጋው ዘገባ ለመረዳት ተችሏል።

ሃብታሙ እና ባልደረቦቹ ባደረጉት ጥናት ደግሞ በከተማም ሆነ በገጠር ሴቶች ከወንዶች በላይ በቀን ብዙ ሰዓት እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል። የከተማ ሴቶች ከ 8 እስከ 13 ሰዓት ሲሰሩ የገጠር ሴቶች ደግሞ ከ 8 እስከ 18 ሰዓታት በስራ ላይ ይሰማራሉ። ያም ሆኖ ግን የሴቶች መጣርና መጋር ወንዶች ለቤተሰብ ከምያደርጉት የገንዘብ መዋጮ (ስጦታ) ሲነጻጸር ዋጋ እንደሌለው ነው የሚቆጠረው።

እርጅና በመጣ ጊዜ ብዙ ሴቶች ዕድሚያቸው ከ50 በላይ የሆኑትን በኢመደበኛ ስራ ላይ ይሰማራሉ፣ ለዚሁ ዋና ምክንያት ደግሞ ፍች ወይም ባሎቻቸውን የሞቱባቸው ሆኖ አንዳንዱ ደግሞ በአይድስ ለተቀዘፉ ወላጆች ልጆች ይንከባከባሉ። በሌላ አነጋገር በርካታ ሴቶች የልጅ ልጆቻቸውን በማሳደግ ላይ ይገኛሉ።

በትምህርት ረገድ 15 ከመቶ በአንደኛ ዲግሪ ሲመረቁ 8 ከመቶ ደግሞ በሁለተኛ ዲግሪ መመረቃቸውን የትምህርት ሚኒሰትር የ2003 ዓ.ም. ዘገባ ያመለክታል። ባጠቃላይ ሴቶች በገቢ ምንጭ ይሁን በሕዝብ ግልጋሎት እኩል ተሳትፎ የላቸውም። ይህ በእንዲህ እንዳለ የተከለሰው የፌደራል ቤተሰብ ሕግ በመንግሥት ትእዛዝ በ2000 ዓ.ም. ወጣ፣ ክልሎቹም የፌደራል መንግሥትን ፈለግ በመከተል የቤተሰብ ሕግጋት አወጡ፦ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ደንብ አዋጅ ቁ. 79/2003፣ የቤኒ/ሻንጉልና ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ደንብ አዋጅ ቁ. 63/2004፣ የኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ደንብ አዋጅ ቁ. 69/2003 እና ቁ. 83/2003፣ የድቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ ብሔሮችና፣ ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት ደንብ አዋጅ ቁ. 75/204። የኦሮምያ ክልላዊ

መንግሥት ሁለት ጊዜ የቤሰብን ደንብ ሲያውጅ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ደግሞ ከፌደራል መንግሥቱ አዋጅ በፊት የቤተሰብ ደንብ አዋጅ ቁ. 33/1999 አወጥቶ ነበር።

ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱትን የቤተሰብ ሕግ ደንቦች ቢታወጁም እንኳ እስከ 2005 ዓ.ም. የገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ቤተሰብና ጾታን በሚመለከት ጥርት ያለ የፖለቲካ ርእዮተዓለም ወይም ስትራተጂ እንደልነበረው የጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት በ2007 ዓ.ም. ገለጻ አድርጓል። "አሁንም ቢሆን" ትላለለች ሰምሃል "አብዮታዊ ዴሞክራስያዊ ርእዮተዓለም ባለው ጊዜ የፆታ ግንኙነት ችግርና የመፍትሔ እርምጃዎች ጥርት ያለ ግንዛቤ የለም።" በተጨማሪም ሰምሃል ባደረገችው ጥናት ላይ የፆታ ልዩነት የገቢ ምንጭ ችግር ለመፍታት ከተፈለገ የፖለቲካ ወረቀቱ እንዳመለከተው ከሆነ "ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት በልማት ዘንድ በሚያደርጉት የተሳትፎ መጠን ነው"። ነገር ግን "የተሳትፎ መጠን" በግልጽ ስላልተቀመጠ የሴቶች የወሊድና የሕጻናት እንክብካቤ ከአገባብ ውጭ ወድቆ ይቀራል።

የሴቶችን ችግር አስመልክቶ መፍትሔ ይሆናል ተብሎ ለጠቅላላ አፍሪቃ የቀረበው 'የስብአዊና የሕዝቦች መብቶች በሴቶች መብቶች በአፍሪቃ' የተሰኘውን ፕሮቶኮል ነው። ይህ የሕግ ሰነድ በ2003 ዓ.ም. በማፑቶ ድጋፍ ካገኘ በኋላ ሊተገበር የጀመረው ግን በ2005 ዓ.ም. ነው። ሰነዱ የአፍሪቃን መንግሥታት በሕግ አውጪ ዘርፎቻቸው አማካኝነት ሴቶች በጋብቻ፡ በገቢ ምንጭ፡ በንብረት ወዘተ እኩልነት እንዲኖራቸው እንድያውጁ አጥብቆ አስገነዘበ።

በኢትዮጵያ ሕጋዊ ረቂቅ ችግር እንዳለ ሰምሃል በጥናታዊ ጽሑፏ ገልጸዋለች። በፍትሕ ሚንስተርና በፌደራል የሕግ ማሻሻያ ጥናት ተቋም መሃል የስልጣን ሽኩቻ እንደነበረም ገልጸዋለች።

### መ. የኮረዳዎች አርግዝና ማሕበራዊ ችግር

የኮረዳ ወይም ወጣት ሴቶች የእርግዝና ማሕበራዊ ችግርን አስመልክቶ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበችው አስቴር በርሀ ነች። በጥናቷም መሰረት ከ 10 እስከ 24 ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ወደ አዋቂነት የሚሸጋገሩ በኢትዮጵያ ታሪክ ወስጥ ግዙፍ ስብስብ መሆናቸውን ተረጋግጧል። ይህ ሰብስብ በቁጥር 21 ሚልዮን ሆኖ ከጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ 30 በሞቶ መሆኑ ነው።

በ2003 ዓ.ም. በተደረገው ጥናታዊ ጽሑፍ እንደተመለከተው 33 ከመቶ ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉት ወጣቶችና በትምህርት ቤት ዙርያ ያሉትን 25 ከመቶ ወጣቶች ዕድሜአቸው 15 ከመድረሱ በፊት በግብረስጋነት እንደሚሳተፉ ታውቋል። ሌላው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አስመልክቶ በተደረገው ጥናት ደግሞ ከተጠኑት ስብስቦች 30 ከመቶ በግብረስጋነት ብርቱ እንቅስቃሴ እንደምያደርጉ ለማወቅ ተችሏል። ይህ የወጣቶች ብርቱ የግብረስጋነት ተግባራት በወጣት ሴቶች ወይም ኮረዳዎች ላይ የማይፈለግ ወይም አስፈላጊ ያልሆነውን እርግዝና ስለሚያስከትል፣ በሕብረተሰቡም ዘንድ ተቀባይነት ስለማያገኝ፣ ኮረዳዎቹ ጽንሱን ለማስወረድ ይገደዳሉ። የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በ2006 ዓ.ም. ባደረጋው ሃገር-አቀፍ ጥናት ላይ

አስተማማኝ ያልሆኑ የጽንስ ማስወረጃ ዘዴዎች ለ55 ከመቶ የእናቶች ሞት እንዳስከተለና ከነዚሁም 13 በመቶ ሴቶች ዕድሚያቸው ከ20 በታች መሆኑን አሳይተዋል።

ግብረስጋነት የሚስከትላቸው ጫናዎች ውስብስብ ያሉ ናቸው። ለምሳሌ የእርግዝና መከላከያ አጠቃቀም አስመልክቶ የከተማ ሴቶች ከገጠር ሴቶች ጋር ሲነጻጸር የከተሞቹ በአምስት እጥፍ እንደሚበልጧቸው ሲታወቅ፣ ባጠቃላይ ሲታይ ደግሞ ለማያስፈልግ እርግዝና የሚያበረክቱ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የተወሰነ የግብረስጋ ስነልቦናዊ እውቀት
- ቀደም ብሎ ማግባት
- የእርግዝና መከላከያ አጠቃቀም ውስንነት
- ለወሊድ መረጃና ትምህርት የተወሰነ ግባት
- ልጃገረዶች በግብረስጋ ህይወታቸው ላይ የሥልጣን ውስንነት

ከማያስፈልግ እርግዝና ምክንያቶች ሌላው ተጨማሪ ምክንያት በሕብረተሰቡ ዘንድ ግብረስጋን አስመልክቶ በግልጽ መናገር ፍላጎት እንደሌለና ለወጣት የወሊድ ፕሮገራም ደግሞ እንቅፋት ለመሆኑ ነው። ከዚሁ ከባህላዊ አመለካከት ባሻገር ባሁኑ ጊዜ በኢትየጵያ የኮረዳዎች እርግዝና ሊባባስ የቻለው በድህነት፣ ብቁ ባልሆኑ የጤና ግልጋሎት፣ በስራ አጥነት፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሕዝብ መፍለስ፣ እና የስእላዊ ግብረስጋነት (pornography) መስፋፋት ናቸው።

የኮረዳ እርግዝና ብዙ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ከነዚሁም አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- በእርግዝና የሚመጣ ከፍተኛ የደም ግፊት
- የተሰናከለና የሚዘገይ ምጥ
- ዝቅተኛ የህጻን ሚዛን
- ደም ማነስ
- ጽንስ ማስወረድ

በጅማ ሆስፒታል በተደረገው የጽንስ ማስወረድ ጥናት እንደሚያመለክተው ደግሞ 57.5 ከመቶ በ15 እና 20 ዕድሜ መካከል ያሉትን ኮረዳዎች ሲሆን ከነዚሁም 35 በመቶ ተማሪዎች ናቸው። የኮረዳ እርግዝና ችግር ለመቅረፍ በማለት መንግሥት በ2004 ዓ.ም. የሃገራዊ ወጣት ፖሊሲ፣ በ2006 ዓ.ም. የሃገራዊ የወሊድ ጤና ስትራተጂ እና በ2007 ዓ.ም. ደግሞ የሃገራዊ የጎረምሳ/ኮረዳ እና ወጣት የወሊድ ጤና ስትራተጂ አዋጆችን አወጣ።

*ሠ. እናታዊ ሞት በኢትዮጵያ*

ለእናታዊ ሞት ጥናት ያቀረበችው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማሕበራዊ ደኅንነት ክፍለ ትምህርት ተማሪ የሆነችው ሜሮን አበበ ነች። በጥናቷም እንደተዘገበው የእናታዊ በሽተኝነትና ሞት በኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ቦታ እንደሚይዝና

በ2000 ዓ.ም ከ10,000 በሂወት የሚወለዱ ህጻናት 816 እንደሚቀጩ ታውቋል። ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ድሃና ትምህርት የሌላቸው 24,000 በገጠርና በቆሻሻ የከተማ ሰፈር አከባቢ የሚኖሩ ሴቶች በቀጣይነት በየዓመቱ በእርግዝና እና በምጥ ጊዜ ይሞታሉ።

የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በ2005 ዓ.ም. እንደዘገበው ደግሞ በሃገር ደረጃ ከአብላጫ ሴቶች 60 ከመቶዎቹ የቅድመ-ወሊድ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው አይጠይቁም፣ 6.3 ከመቶ ብቻ ደግሞ ከድሕረ-ወሊድ በኋላ በመጀመርያው ስድስት ሳምንታት እንክበካቤ ይደረግላቸዋል፣ 9.7 ከመቶ ብቻ ችሎታ ባላቸው በለሙያዎች እርዳታ ይወልዳሉ። ከ 85 ከመቶ በላይ ግን በልታወቁና በባህላዊ አዋላጆች ወይም ዘመድ እርዳታ ነው የሚወልዱት።

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች እናታዊ ሞት ወይም የአዲስ ህጻን ሞት እንደ ባህርያዊ ወይም ተፎጥሮአዊ አድርገው ነው የሚያዩት። ስለሆነም ለእናታዊ ሞት ምክንያት ከሆኑት እንደ ቀድሞ ማግባትና መውለድ፣ ግዝራት፣ አድልዎ አመጋገብ ለሴቶችና ልጃገረዶች፣ ራስን አዋላጅ መሆን፣ ንጽህና የሌላቸው የእትብት እንክባከቤ እና ዘግይቶ ጡት ማጥባት ተግባራት በሰፊው ይዘወተራሉ። የአንድ ሕብረተስብ ማሕበራዊ ችግሮች ለመረዳት 'ተግባራትን' ማጤን አስፈላጊ ነው ያለው ቪበር ትክክል መሆኑን እንገነዘባለን።

ለእናታዊ ሞት በኢትዮጵያ ዋናዎቹ አምስት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፦

1. ጽንስ ማስወረድ (32%)
2. የተዛባ ምጥ (22%)
3. ቁስል (12%)
4. በሰውነት ውስጥ ብዙ ደም መፍሰስ
5. ከእርግዝና ጋር የተያያዘ ከፍተኛ የደም ግፊት (9%)

(ጤና ጥበቃ ሚኒስተር 2003 ዓ.ም.)

ሌሎች 15 ከመቶዎቹ ደግሞ ኢቀጥታዊ በሆኑ ምክንያቶች ነው የሚፈጸሙት። ለምሳሌ በቆየው ሕመምና እና በእርግዝና ጊዜ ወይም በምጥ ጊዜ የተባባሰ፣ ወባ፣ የደም ማነስ፣ የጉበት ብግነት እና አይድስ ደግሞ ለእናታዊ ሞት ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው።

ከዚሁ ጥናት ጋር የሚያያዝ "አደገኛ የጽንስ ማስውረድ እንደ ማሕበራዊ ችግር" በሚል ርእስ ሌላ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበች ሰብለወንጌል ዓይንአለም ነች። ጽሑፉ በ2008 ዓ.ም. ለማሕበራዊ ደኅንነት ድሕረ-ምረቃ ክፍለ-ትምህርት የቀረበ ነው። 'የኢትዮጵያ የወሊድና የማህጸን ሃኪሞች ማሕበር' በ2001 ዓ.ም. ባቀረበው ዘገባ ከ 3.21 ሚልዮን እርግዝና 500,000 ድንገተኛ ወይም አደገኛ ጽንስ ማውረድ ያደርጋሉ። በጥናቱም መሠረት በጋምቤላ ከ 3 እስከ 4 ያላለቁ/ያልተሟሉ የጽንስ ማስውረድ ሙከራ በየቀኑ ወደ ክልላዊ ሆስፒታል ያመራሉ፣ በአክሱም ቅድስት ማርያም ሆስፒታል ያላለቁ/ያልተሟሉ 15 የጽንስ ማስውረድ ሙከራዎች በየወሩ ይመጣሉ፣ በባህርዳር ፈለገ ህይወት ሆሰፒታል ደግሞ እንደዚሁ ከ 2 እስከ 3

ያልተሟሉ ጽንስ ማውረድ ሙከራዎች በየቀኑ ወደ ሆስፒታሉ ይመጣሉ። ይኸንን ማሕበራዊ ችግር አስመልክቶ ዩሱፍና ዜን የተባሉ "የጽንስ ማስውረድ በጎንደር ኮለጅ ሆስፒታል፡ ኢትዮጵያ" በሚል ርእስ ለምስራቅ አፍሪቃ የሕክምና መጽሔት በ2001 ያሳተሙት ጥናታዊ ርእሰ-ነገር ቀርቧል።

ለዚሁ ለእናታዊ ሞትና አስፈለጊ ያልሆኖውን ጽንስ ችግር ሊወገድ የሚችለው ግን ሰፋ ባለ መልኩ ህዝቡን ስለ ግብረስጋና ጥንቃቀዎች ማሰተማርና በየትምህርት ቤቱ ደግሞ የትምህርት ዓይነት አካል ሆነ ሲቀርብ ብቻ ነው። በ2008 መንከባከብና ማስውገድ ያለብን ባህሎች በሚል ርእስ በደረስኩት መጽሐፌ ውስጥ "ግብረስጋና ጥንቃቄ" በሚል ምዕራፍ ይኸንን ማሕበራዊ ችግር ከነመፍትሔው ለውይይት አቅርቤዋለሁ።

ባለፉት አራት ወይም አምሰት ዓመታት ግን የጤና ጥበቃ ማሕበራዊ ችግር በጦፈና በሰፊው በመላው ኢትዮጵያ በቀዳማይ ጤና አጠባበቅ (primary healhcare) አትኩሯል ማለት ይቻላል። የጤና ቅጥያ (health extension) ባለሙያዎች በገጠር የጤና አጠባበቅ ዘዴ (hygiene) ትምህርትና እርዳታ እያደረጉ ነው። ዓላማውም ሕዝቡ በሚገባው መሰረት፡ ለምሳሌ በመሃል ኢትዮጵያ 'አስቀድሞ መጠንቀቅ ኋላ ከመማቀቅ' (የኔ ሐርግ ነው) በሚል ቢሂል አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንድያደርግ ህዝቡን እያስተማሩ ነው። በተመሳሳይ መልኩ በትግራይ ክልል "ጽሬት ካብ ድሙ ንመሃር" (ጽዳትን ከድመት እንማር) በሚል መርሆ በሕዝቡ መሃል ከፍተኛ የጤና አጠባበቅ ዘዴ ዘመቻ እያካሄዱ ነው። ሰዎች በተለያየ ጊዜ እጃቸውን እንዲታጠቡ፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱ ሽንት ቤት እንዲኖረው፣ ከብትና ሰው የተለያየ መጠለያ እንዲኖራቸው፣ ያረገዙ ሴቶች በየወሩ እንዲመረመሩ፣ በቡና ጊዜም ሁልጊዜ ስለ ጤና አጠባበቅ መረጃዎች እንዲቀያየሩ ወዘተ እየተደረገ ነው። የጤና ቅጥያ ስራ በዚህ መልኩ ከቀጠለ የእናታዊ ሞት እና ያልተፈለገ የኮረዳ እርግዝና ከመከላከል አልፎ ለአጠቃላይ የሕዝቡ ጤንነት ከፍተኛ አስተወጽኦ ይኖረዋል።

ረ. የወጣት ሥራ አጥነት ችግር በአዲስ አበባ

ለዚሁ ርእስ ነገር ጥናተዊ ጽሁፍ ያቀረበው በአዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ ማሕበራዊ ደህንነት ክፍለ-ትምህርት የድሕረ-ምረቃ ተማሪ ተመስገን አሰፋ ነው። በጥናቱም እንዳመለከተው ስራ አጥነት በኢትዮጵያ ከተሞች ከፍተኛ ችግር መሆኑን ነው። ከጠቅላላ ስራ አጥ ኢትዮጵያውያን 67 ከመቶ ወጣቶች ናቸው። የወጣት፡ ስፖርትና ባህል ሚኒስተር በ2004 ዓ.ም. እንደዘገበው ከሆነ ደግሞ 44 ከመቶ ኢትዮጵያውያን ከድህነት በታች እንደሚኖሩና ከነዚሁ በጠና የተጠቁት የሕብረተሰቡ ክፍል ደግሞ ወጣቶች ናቸው።

የወጣቶች ማሕበራዊ ችግር በሚመለከት ውይይት ተካሂደው ነበር። በውይይቱ እንደተመለከተው ወጣቶች ተንቋል፣ ከዚሁም የተነሳ ቀቢጸ-ተስፋነትን ያጠቃቸዋል፣ ለዚሁም ዋና ምክንያት በሃገሪቱ የተከሰቱትን የፖለቲካ፡ ማሕበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ችግሮች ናቸው። ችግሩን ለመወጣት ደግሞ በ2006 ዓ.ም. 'የኢትዮጵያ የከተማ ወጣት የልማት ቅንብር' የሚል ስትራተጂ ተቀይሶ ነበር።

በ2007 ዓ.ም. በማእካለዊ ሰታቲስቲክስ ድርጅት እንደተዘገበው ከሆነ የአዲስ አባባ የሕዝብ ብዛት 3,147,000 ሲሆን ከዚሁ የሕዝብ ቁጥር 1,511,00 ወንዶች ሲሆኑ፣ 1,636,000 ደግሞ ሴቶች ናቸው። ቀደም ብሎ ማለትም በ2003 ዓ.ም. በዚሁ የስታቲስቲክስ ድርጅት ባቀረበው ጥናት ደግሞ ከ1,010,372 ሕዝብ ወንድ 345,900 (34.23 ከመቶ) እና ሴት 664,472 (65.77 ከመቶ) ስራ ፈት ናቸው። ከነዚሁ ስራ ፈቶች ደግሞ በ 15 እና 29 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ከጠቅላላ 983,428 ሰዎች 423,055 (43 ከመቶ) ወንዶች፣ 560,373 (57 ከመቶ) ሴት ወጣቶች ናቸው። የስራ ፈትነት ወይም ስራ አጥነት ችግር ከጾታ አንጻር ሲታይ ደግሞ በ2005 ዓ.ም. 40 ከመቶ ሴቶች ስራ አጥ ሲሆኑ፣ የወንዶች ስራ አጦች ግን 22.5 ከመቶ ብቻ ነው።

ስታቲስቲክስን በተመለከተ ግን ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ጉዳይ አለ። የሕዝብ ብዛት በየጊዜው ሊቀያር ይችላል፣ ለምሳሌ ባሁኑ ጊዜ ማለትም በ2013 ወይም በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ የህዝብ ብዛት ወደ 89 ሚልዮን ሲገመት የአዲስ አበባ ደግሞ 3,384,569 ነው። በስድስት ዓመት ውስጥ የከተማው ብዛት በ237,569 ጨምሯል። ይህ የሕዝብ ብዛት ግን ኗሪነታቸው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ለሆኑት የሚመለከት ነው፣ የአዲስ አበባ ዙርያ ከተጨመረበት ደግሞ የሕዝብ ብዛት 4,567,857 ይደርሳል። ዱርካይም እንዳመለከተው ስታቲስቲክስ ለጥናት ጠቄሜታ ቢኖሮውም ቅሉ አንዳንዴ ግን ሲ ራይት ሚልስ እንደተነተነው ስታቲስቲክስ ሐቁን ሊሸፍን ስለሚችል ስራ አጥነትን አስመልክቶ በሌሎች ነጻ የሆኑትን ጥናታዊ ጽሁፎች ካቀረቡት ዘገባዎች ጋር ማነጻጸር የግድ ይላል።

ሌላ በዚሁ የስራ አጥነት ችግር ላይ ተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበው ከአዲስ አባባ ዩኑቨሪሲቲ ማሕበራዊ ደኅንነት ክፍል-ትምህርት የድሕረ-ምረቃ ተማሪ ኅጃም ቦጋለ ነው፣ የጥናቱ ትኵረት ደግሞ በተማሪ ወጣት ስራ አጥነት ላይ ነው። የዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት እንዳመለከተው ከዓለም ጠቅላላ ኢትዮጵያ የላቀ የስራ አጥነት ችግር አለባት፣ ከከተማ ኗሪዎች 50 ከመቶ ስራ ፈት ናቸው (ILO 2004፣ 2007)። በ1999 ዓ.ም. በተደረገው የአሰሳ ጥናት 66.57 ከመቶ ወጣት ከተባሉት የሕዝቡ ከፍል 24 ከመቶ የወጣት ምሁራን ናቸው።

የወጣት ምሁራን ስራ አጥ መሆን የሚያስደንቅ አይሆንም፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ባሁኑ ደረጃ መጠነ-ሰፊ ኢንዱስትሪዎች የሏትም። የምጣኔ ሃብቱ ማደግና አጠቃላይ የዕድገት ጉዞ ገና በእንጭጭነቱ ስለሚገኝ የኮለጅና የዩኒቨሪሲቲ ምሩቃን በቀላሉ ማስተናገድና ዝግጁ ስራዎችን ማበርከት አይቻልም፣ ግን ባለፉት ሦስት ዓመታት መንግሥት ለአዳዲሰ ምሩቃን ራሳቸውን ስራ እንዲፈጥሩ ለማበረታታት ያህል ለእያንዳንዱ ምሩቅ የ20 ሺ ብር ድጎማ በመስጠት በልዩ ልዩ ንብረተ-ተቋማት እንዲሰማሩ እያደረገ ነው።

ሰ. ጫት ቃሚ ወጣት በኢትዮጵያ

ለዚሁ ማሕበራዊ ጉዳይ ጥናተዊ ጽሑፍ ያቀረበው ከአዲሰ አበባ የኒቨሪሲቲ ማሕበራዊ ደኅንነት ክፍለ ትምህርት ማርታ አለማየሁ ነች። በጥናቷም እንዳሳየችው ጫት ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚበልጥ ነው፣ የሚያስከትለውን አሉታዊ ውጤት ደግሞ

በዝርዝር አቅርበዋለች፦

- ለረጅም ጊዜ ጫት ከተወሰደ መጠነኛ የአንጎል መዛባት ያስከትላል
- በብዛት ከተወሰደ ጸንፈኛ ጥማት፣ ቅብጥብጥነት፣ እንቅልፍ አጥነት፣ እና የፍላጎተ-ምግብ አጥነት ያስከትላል
- በመጠኑም ከተወሰደ ስራ ፍርያማነት ይቀንሳል፣ ምክንያቱም የጫት ቃሚው የፍላጎት ኀሊና ስለሚቀንስ ነው
- በተደጋጋሚ ከተወሰደ ደግሞ ቅዠትና የአእምሮ የመደናገርን በሽታ ያስከትላል
- ጫት በተጨማሪ ጅማቶችን፡ የትንፋሽ፡ የደም ዝውውር፡ እና የምግብ መንሸራት ስርዓቶችን ይጎዳል።

ለጫት ማሕበራዊ ችግር እንደ መፍትሄ የቀረበው በሕግ በአዋጅ መንግሥት ወጣቶች ጫት እንዳይገዙ፣ ሻጩም እንዳይሸጥላቸው መከልከል አለበት የሚል ነው። በተጫማሪም መንግሥት ክትትል በማድረግ ለጫቱ ገበያነት አመቺ ሁኔታ እንደማይኖር ማረጋገጥ አለበት የሚል ነው። ይህ ግን የዘሌቄታ መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም፣ በመጠኑ የጫት ቃሚ ወጣቶች ቁጥር ሊቀንስ ይችላል፣ ሙሉ በሙሉ ግን መቆጣጠርና ችግሩን ለመፍታት አይቻልም፣ ምክንያቱም የጫት መቃም በተለይም በአንዳንድ የኢትዮጵያ አከባቢ እንደ ሃረር ወይም ጅማ የመሳሰሉት ጫት ከባህላቸው ጋር የተቆራኘ ስለሆነ የጫትን አሉታዊ ጎኑ አያዩትም። ከዚህም በላይ በብዙ የደቡብ ኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች ጫት እንደ አንድ የገቢ ምንጭ ያገለግላል።

ስለሆነም የጫት ማሕበራዊ ችግር ለመፍታት ከተፈለገ መንግሥት ሕግ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የጠፈ ትምህርት በትምህርት ቤቶችና በብዙሃን መገናኛዎች አማካኝነት ሕዝቡን ማስተማር አለበት።

## II. የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት በኢትዮጵያ፡ ምሳሌዎችና ፍጆታ ዋጋዎች

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከሞላ ጎደል ከሊ ባንከርስ እና ዶግላስ ወብ የተባሉት የዩኒሰፍ ወይም የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የሕጻናትና ትምህርት ፋንድ ወኪሎች በ2011 ዓ.ም. ባቀረቡት ዘገባ ላይ የተመረኰዘ ነው። ጥናቱ የሚከተሉትን ዓበይት ርእሰ-ነገሮችን ያካትታል፦

- የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት በዕድገትና ለውጥ (ትራንስፎርመሽን) እቅድ
- አገር-አቀፍ የማሕበራዊ ልማት የገንዘብ ምንጭ
- የልማታዊ-ማሕበራዊ ደኅንነት ፖሊሲ ክለሳ
- ቤተሰብን መሰረት በማድረግ በአማራጭ የሕጻናት እንክብካቤ መዋቅሮችና ሥርዓቶች ላይ ተጨማሪ ትኵረት ማድረግ
- የባህላዊ ደጋፊ ዘዴዎችን እንደገና ማሳደስ

የማሕበራዊ ደኅንነት በፍትሕ ዘርፍ አስመልክቶ ደግሞ የሚከተሉትን ነጥቦች

ወይም ክንውኖችን ያካትታል፦

- የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ የማሕበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ አስፈላጊነት፣ ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉትን ስብስቦች
- የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አማካሪ ቡድን አቋቁሟል፣ የሕጻናትን ጉዳይ በተመለከተ ዳኞቹን የሚረዱ 20 የማሕበራዊ ደኅንነት ሰራተኞች ተቀጥረዋል
- ዩኒሰፍና የአዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ የማሕበራዊ ደኅንነት ትምህርት ቤት ለሥርዓቱ ምሳሌዎችን ለማቅረብ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር በመተባበር ላይ ይገኛሉ
- በፍርድ ቤት አማካሪ ቡድን ሥር ላይ የተመሰረተ ማሕበራዊ ደኅንነቶች ለፖሊሲ፡ ለማረምያ ማእከሎች እና ለፍትሃብሄርና ወንጀለኛ መቅጫ ዳኞችም እርዳታ ያደርጋሉ
- የማሕበራዊ ደኅንነት ሰራተኞች ማሰልጠንና አስፈላጊውን ቋሚ መምርያ ማውጣት። እንዲሁም ሞያተኞች በፍርድ ቤት ውስጥ እንዲሰሩ መደበኛ መዋቅር መገንባት

የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት በዕድገትና ለውጥ (ትራንስፎርመሽን) እቅድ 2011-2015

ያገሪቷ ምጣኔሃብትና ማሕበራዊ ልማቶች በሚደራጁበት ጊዜ በተጻከሙና አረጋውያን ሰዎች መብት በአጽንኦት እንዲጠበቅ ያደርጋል። እንደ ግለሰቦች ከሌሎቹ ሰዎች በመተባበር ችሎታቸውን ለማሕበራዊ ልማት እንዲያበረክቱና በፖለቲካ፡ ምጣኔሃብተዊና ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ረገድ ራሳቸው ለመደገፍ እንዲችሉ ያደርጋል።

የማሕበራዊ ደኅንነት ፕሮግራሞች የሚያካትቱት ቤተሰብና ሕበረተሰባዊ መሰረት ያላቸው፣ መንግሥትና የመንግሥት ተቋም ያልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት መደበኛ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ፣ ወይም ደግሞ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ማሕበረሰቦች ኢ.መደበኛ በሆነ መንገድ እርስ በራሳቸው እንዲደጋገፉ የሚጥሩ ድርጅቶች ናቸው።

የዘርፉ ንድፍ ዓላማ የአገሪቷ የማሕበራዊና ምጣኔሃብታዊ ሂደት ለማቀላጠፍ ሆኖ ድርሻ ያላቸው ሰዎች ደግሞ የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት እንዲደራጁ ፣ የአገሪቷ ደኅንነት ለማቀላጠፍ እንዲረዱና አካለስንኩሎችና አረጋውያን የሚጠቀሙበት መንገድ እንዲቀይሱ ነው።

በጥናቱ ለማሕበራዊ ደኅንነት ሥልጠና የተጠናቀሩ ርእሰ-ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦

- የህጻናት ደኅንነት፣ አይድስ፣ ስነልቦናዊ/ማሕበራዊ እና መንፈሳዊ ድጋፍ
- ኤች አይ ቪ እና አይድስ ስነልበናዊ/ማሕበራዊ ድጋፍ
- የህጻናት ደኅንነትና ጥበቃ፣ መሠረታዊ መስተዳድርና የቤተሰብ ድጋፍ
- ልማትን መሠረት ያደረገ የህጻናት ደኅንነት የሚያጠና ማሕበረሰብ

- ማሕበራዊ ደኅንነት በፍትሕ ዘርፍ፣ ግብረገብና ወጎች
- የማሕበራዊ ደኅንነት እውቀትና ተግባር
- የማሕበራዊ ደኅንነት ሂደትና ሙያ
- ማሕበራዊ ደኅንነትና ሕግ
- ማሕበራዊ ደኅንነት፣ በተለይም በኤች አይ ቪ/ኤይድስ እንክብካቤና ድጋፍ ያለው ሚና

ማን ነው በሥልጠናው የሚሳተፍ?

- የአንደኛ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያላቸው የማሕበረሰብ ፈቃደኞች
- 12ኛ ክፍል ያገባደዱ ሁሉ
- ቢያንስ ቢያንስ 10ኛ ክፍል የጨረሹ፣ የሙያ ተመክሮ አይጠየቅም!
- የመግሥትና መንግሥት ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞች
- ከማሕበራዊ ደኅንነት ጋር የተያያዘ ቢያንስ ቢያንስ የሁለት ዓመት ተመክሮ ያላቸውና የአንደኛ ዲግሪ ያላቻው በለሙያ ሠራተኞች

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ሰልጣኞች በክልላዊ መንግሥታትና በተባበሩት መንግሥታት ወይም የመንግሥት ያልሆኑ የአለምአቀፍ ድርጅቶች ይቀጠራሉ።

ባጠቃላይ በሦስት ዓመት ውስጥ 654 የማሕበራዊ ደኅንነት ሠራተኞች ሰልጥነዋል፣ 150 ሰዎች የማሕበራዊ ድሕረ-ምረቃ ዲግሪ አገባድደዋል፣ 80 ደግሞ የማሕበራዊ ደኅንነት የመጀመርያ ዲግሪ ለማገባደድ በሂደት ላይ ናቸው፣ አንድ ሰው ደግሞ በማሕበራዊ ደኅንነት የዶክተር መዓርግ አግኝቷል።

የሥልጠናው ይዘት ሁሉም የማሕበራዊ ደኅንነት መርሆዎች እንደ ግብረገብ፡ ወግ፡ የኤች አይ ቪ/ኤይድስ እንክብካቤና ድጋፍ፣ ማሕበረሰባዊ እድገት፣ የሕጻናት ደኅንነት፣ ሕብረተሰባዊ ጥናት፣ ቤተሰብን መርዳት ያጠቃልላል።

የማሕበራዊ ደኅንነት ሰራተኞችና ጥገኛ ሰራተኞችን ለማሰልጠን በአንድ ዓመት ውስጥ ከ 5ት እስከ 24 ቀን ይፈጃል፣ አማካይ ጊዜ 20 ቀን ነው። የስልጠናው ትኵረት በከተሞች አከባቢ ሆኖ በተለይም በአዲስ አበባ ላይ ያተኰረ ነው።

ፍጆታ ዋጋ

- ለያንዳንዱ ተማሪ ዋጋ የሚወጣው ከ $80 ዶላር እስከ $5500 ዶላር ነው
- በዝቅተኛ ደረጃ፡ ማለት ከ 5-8 የስልጠና ቀናት የስልጠናው ቦታ ወጋ ሳያካትት
- በከፍተኛ ደረጃ የአንድ ዓመት ሥልጠና፡ ለተሳታፊ ሰልጣኞች የመጓጓዣ ዋጋና በ$150 የሚገመት ወርሐዊ ደመወዝ ለ15 ወራት፣ ደመወዙ ሳይጨምር ለስልጠናው ብቻ በግምት $2250 (ወይም $150 በወር ለእያንዳንዱ ተማሪ)። ይኸም የስልጠና ስነትምህርት፣ አሰልጣኞች፣ የስልጠና መሳርያዎች፣ መጓጓዣ፣ ማረፍያ ቦታዎችን ይጨምራል
- የማሕበራዊ ደኅንነት የመጀመርያ ዲግሪ ስልጠና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለአንድ ተማሪ ምኝታና ምግብ ጨምሮ (3-4 የዓመት ፕሮግራም) ይጨርሻል፣ ወይም $750 ለጠቅላላ ፕሮግራም ($200 ለአንድ ተማሪ ለአንድ ዓመት)

- የድሕረ-ምረቃና የዶክትሬት - 500 ብር ለአንድ ክሬዲት ወይም $1250 ለአንድ ተማሪ በዓመት

ለእያንዳንዱ ወረዳ (ባሁኑ ጊዜ 801 ወረዳዎች አሉ) በዓመት $1.2 ሚልዮን ዶላር ዋጋ ሲገመት በከፍተኛ ግምት ደግሞ ወደ $8.8 ሚልዮን ዶላር ይጠጋል። በዚሁ ጥናት በቅጡ መረዳት የተቻለው የሕጻናት እንክብካቤ አማራጭ መንገዶች ያለመኖራቸውና ፕሮገራሙ በከተሞችና በአዲስ አባባ ብቻ ማትኮሩ የፕሮግራሙ ደካማ ጎን ያሳያል።

## III. እርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ

ለዚሁ ጥናት መነሻ ሰነድ ያቀረቡልን የማሕበራዊ ጥበቃ ማእከል አባለት የሆኑትን ስቲቭን ደቭሮ እና ብሩስ ጋትነር ናቸው። ጽሁፉ በ2009 ዓ.ም. ነበር የቀረበው፣ ለዚሁ ርእሰ-ነገር ግን አሁንም ቢሆን ጠቁሜታ ስላለው በመነሻ ሰነድ የቀረቡትን ዓበይት ነጥቦች እንደ 'እርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ'፣ 'የመሬት ፖለቲካና ማሕበራዊ ጥበቃ'፣ 'የእርሻ ልማት ስትራተጂ'፣ 'የምግብ ዋስትና (ደኅንት) ፕሮግራም'፣ 'ሌሎች ማሕበራዊ ጥበቃዎች' እና 'ትናንሽ እርሻዎች' በተመለከተ ከሞላ ጎደል በዚሁ ምዕራፍ ይቀርባሉ።

ይህ ምዕራፍ በጥበቃና ዋስትና ያተኮረ ነው፣ ከአጠቃላይ የእርሻ ልማትም መምታታት የለበትም። የእርሻ ልማትን አስመልክቶ በ 'ዲሞክራሲ፣ስልጣን ማከፋፈልና ልማታዊ መንግሥት' (በእንግሊዝኛ የተጻፈ) በተሰኘው መጽሐፌ ውስጥ በዝርዝር ስላቀረብኩት እዚሁ ማሕበራዊ ገጽታውን ብቻ ነው የማቀርበው።

ደቭሮ እና ጋትነር "እርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ እጅግ በጣም የተቆራኙ ናቸው" ይላሉ። በተጨማሪም፡ ትናንሽ እርሻዎች የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮን ያንጸባርቃሉ። በሌላ በኩል ግን፣ ትናንሽ እርሻዎች የድህነት አደጋነትን፡ ያለጊዜ መቀጨትን፡ እና ለተደጋጋሚ ረሃብ መጋለጥን መንስኤ መሆናቸውን እንረዳለን።

ድህነትን ለማጥፋት መንግሥት አራሹ ከኋላ ቀር የእርሻ ዘዴና ከውጭ እርዳታ እንዲላቀቅና ወደ ገንዘብ ማመንጫ ዘዴዎችን እንዲሰማራ በማለት ከንግድ ጋር የተያያዙ እርሻዎችን እንዲያጕለምስ በማለት 'ፈጣኝና ቀጣይ የልማት ንድፍ' እና 'የምርት ዋስትና ፕሮግራም' የተባሉትን ስትራቴጂዎችን አወጣ። የምርት ዋስትና ፕሮግራም ለኋላ ቀር እርሻዎች ገንዘብ ይሰጣል፣ የልማት ንድፍ ደግሞ የገበያ ትስስርና ወደ ውጭ የሚላኩ እህሎችን በማሳደግ በይበልጥ ገንዘብ እንድያመነጩ ይረዳል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱቱን የመንግሥት አነሳሽነት ግን ያልተጠበቀ አሉታዊ ጣልቃገባነትን ፈጥረዋል። እርዳታ በተደረገበት ቁጥር ገበሬዎች እርሾቻቸውን

እርግፍ አድርገው በመተው ለእርሻ ስራዎች ላይ በተዳከመ መልኩ ነው የተሰማሩት። መሆን የነበረበት፣ ወይም እንደ መፍትሂ መቅረብ የነበረበት በማለት በሐሳብ ደረጃ የቀረበውን፡ ግን በግብር ያልዋለውን፡ ለገበሬዎች የሚሰጠው ክፍያ የእርሻ ወራት ከመጀመራቸው በፊት መሆን ነበረበት የሚል ነው። በተጨማሪም አደጋን ለመቅረፍና ለመቆጣጠር የወጣ ሃገራዊ መምርያ ፖሊሲ በግብር ለመተርጎም ከተፈለገ በገጠር ለሚደረጉ የማሕበራዊ ደኅንነት ስራዎችን እጅግ ደካማ መሆናቸውን ታውቆ፣ ማሕበራዊ ጥበቃ ፕሮግራም የስራ ቅድመ ሁኔታ መሆን የለበትም።

ሌላው መደረግ ያለበት የእርሻ ዝቅተኛ ግባትና ዝቅተኛ ውጤት በሚከሰትባት ጊዜ ፖሊሲ አውጭው የምርት ውጤታቸውን በይበልጥ ለማሳደግ አነስተኛ ገበሬዎችን ማበረታታት አለበት። ይኸም የ'ሳሳካዋ ዓለም አቀፍ 2000' በተመለከተ ሆኖ ማዳበርያና ምርጥ ዘሮችን ለገበሬዎች በተፈራረቀ ዱቤ አማካኝነት እንዲሰጥ ማድረግ ነው። ይህ ውጥን በብዙ አገሮች፣ ኢትዮጵያም ጭምር፣ ስኬታማ ሆኗል።

ነገር ግን በ1990ዎቹ የሳሳካዋ ዓይነት እርዳታ የተደረገላቸውን የኢትዮጵያ ገበሬዎች በድርቅና መጥፎ አዝመራ ምክንያት ዕዳቸውን መክፈል ያልቻሉትን እንዲታሰሩ ተደርጓል። ለዚሁ የትናንሽ ገበሬ እርሻዎች መፍትሔ የሚሆነውና እኔም በመጻሓፌ ያሰመርኩበት፣ ደቭሮ እና ጋትነርም የሚደግፉት፣ የመስኖ እርሻን ነው። ደግነቱ ባለፉት አስርት ዓመታት የመስኖ እርሻዎች በኢትዮጵያ በስፋት ተዘርግተዋል።

ከእርሻና ከማሕበራዊ ጥበቃ ነጥለን ማየት የማንችል የመሬት ፖለቲካ በኢትዮጵያ አስመልክቶ ነው። ያለፈው የደርግ መንግሥትና አሁንም ያለው የኢሕአዴግ መንግሥት መሬት ለገጠሩ ሕዝብ ዋስትና ነው ብለው ነው የሚያምኑት። ነገር ግን ዋስትና የተባሉትን መሬቶች ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ለልምዳዊ እርሻ ስለሚጠቀሙባቸው፣ ምርቱ ከእጅ ወደ አፍ ስለሆነ፣ የሂወት ማቆያ እርሻዎች እንጂ በአራሹ ሂወት ዘንድ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጡና ለኢትዮጵያ ምጣኔሃብታዊ ድጋፍ ሊሆኑ አይችሉም።

በእርግጥ በደርግ ጊዜ የተደረገውን የመሬት ይዞታ መሻሻል ለማሕበራዊ ደኅንነትና ጥበቃ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው። መሬት ያልነበራቸው ጭሰኞች መሬት አገኙ፣ 'መሬት ላራሹ' በግብር ተተረጐመ። ግን መሬት ብቻ ይዘው የእርሻ መሳርያዎች፣ በሬ፣ የእህል ዘር ያልነበራቸው ገበሬዎች በባሰ ደረጃ ነበር የደኸዩት። ሁሉም ነገር ያሟሉ ገበሬዎችም ቢሆኑ እርሻዎቻቸውን በጣም አነስተኛ ስለሆኑ በዛው መጠን ከድህነት የሚያወጣቸው ጠቃሚ ያለው ንብረት ማፍራት አልቻሉም። እንድያውም በአንዳንድ ቦታ ላይ የመሬት ይዞታ መሻሻል የጋርዮሽ ድህነትን ነበር ያስከተለው።

የኢትዮጵያ ደሃ ገበሬዎች ታድያ ከማሕበራዊ ደኅንነት ወይም ጥበቃነት ይልቅ በ1984 እና በ1993 ለተከሰቱት ረሃቦች ነው ሰለባ የሆኑት። ግን በመጽሐፌ እንደገለጽኩት በኢሕአዴግ 'ጠባቂና ደንበኛ' ግንኙነት አማካይነት በርካታ ገበሬዎች ተጠቃሚ የሆኑ አሉ። ከዚሁ የጠባቂ-ደንበኛ ግንኙነት ባሻገር ግን ኢሕአዴግ መጀመርያ ያወጣውን የልማት ስትራተጂ ማለትም 'በእርሻ-ልማት የተመራ

እንዱስትሪ’ በመተው አዲስ ‘ድህነትን የመቅረፍ ስትራተጂ ወረቀት’ (ድህነትን ለማጥፋት ፈጣንኛ ቀጣይ የልማት ስተራተጂ) መመርያ መሰረት በማድረግ መጠነ-ሰፊ የንግድ እርሻዎች እና በውጭ ምንዛሪ ላይ ያተኰረ ስትራተጂ ቀየሰ። የአዲሱ ስትራተጂ ዋና ዓላማ ደግሞ በአምስት ዓመት የኢትዮጵያ የእርሻ ምርት በአምስት እጥፍ እንድያድግ ለማድረግ ነበር።

በ2007 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት ባወጣው መግለጫ ላይ “የእርሻ ማሕበረሰቦች የድሮ የእርሻ ስርዓትን ትተው የገበያ-አቅጣጫ ዘዴን በመቀበል ሻጭና ሸማችን የሚያበረታታ ብቃት ያለው ስርዓት ማደራጀትና ማስፋፋት አለባቸው” ይላል። ይህ ከበፊቱ መንግሥት አቋም የሚጋጭ ቢመስልም ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ መንግሥት ‘የምግብ ደኅንነት ፕሮግራም’ በማውጣት ከማሕበራዊ ደኅንነት ፕሮግራሙ ብዙ አልራቀም። የምግብ ደኅንነት ፕሮግራም ሦስት ነገሮችን ያካትታል፦ 1) የምርት ደኅንነት ፕሮግራም - የሕዝብ ግልጋሎትና ቀጥተኛ ድጋፍ ንኡስ ክፍሎችን የያዘ፣ 2) የቤተሰብ ቅጥያ ቅንብር፣ 3) የፈቃድ ሰፈራ ፕሮግራም

የምርት ደኅንነት ፕሮግራም ዓላማ ደግሞ የማሕበረሰብ ፀጋዎችን ማነጽና ኑሯቸውንም ማበልጸግ፣ ዋጋ ያለው የቤተሰብ ንብረትን መጠበቅ፣ ርሃብን መከላከል ናቸው።

በ2006 ዓ.ም. በስምንት ወረዳዎች በተደረገው የጥናት አሰሳ ከምርት ደኅንነት ፕሮግራም የምግብ እርዳታ የተደረገላቸው ቤተሰቦች 88 ከመቶ ምግቡን በልተው ሲጨርሹት 7 ከመቶ ደግሞ ገሚሱን ሸጠው የተቀረውን በልተውታል፣ አንዳንድ ቤተሰብ ደግሞ የተሰጣቸውን ምግብ ከዘመዶቻቸው ጋር ተካፍለውታል። ገንዘብም የተሰጣቸው እንደዚሁ 88 ከመቶ ጠቅላላ የተሰጣቸውን ብር ለዋና ምግብ መግዣ ሲያውሉት፥ 11 ከመቶ ደግሞ ለሌላ ዓይነት ምግብ መግዣ አውለውታል። ይኽንን ስታቲስቲክስ ያቀራብልን ደቨሮ ነው።

ነገር ግን በረሃብ ጊዜ የፈለገውን ድጎማ ቢደረግ የገበሬውን ህይወት በቀላሉ ማስተካከልና መቀየር ስለማይቻል ብዙ በምርት ደኅንነት ፕሮግራም የሚደገፉ ቤተሰቦች ንብረታቸውን እንዲሸጡ ወይም መሬታቸውን እንድያከራዩ ተገደዋል። ስለሆነም ድህነትን ለመቅረፍ በተደረገው ጥረት ላይ በከፊሉ ነው ውጤትን ያስገኘው ይላል ደቨሮ።

ሌላ በዓለም የምግብ ፕሮግራም ‘የትውልድ-ስራ ዕቅድ’ ወይም ‘ፕሮጀክት 2488’ በማለት የሚታወቀውን ስር ‘የምግብ-ለስራ ፕሮግራሞች’ በኢትዮጵያ አደራጅቶ ነበር። የመንግሥቱ የምርት ደኅንነት ፕሮግራም ከሞላ ጎደል የዓለም ምግብ ፕሮግራም ፕሮጀክት ቢከተልም ቅሉ ከምግብ ይልቅ በ ‘ገንዘብ-ለስራ’ ነበር ያተኰረው። ይህ እርምጃ የተወሰደውም በ2006 ዓ.ም. የአሰሳ ጥናት መሰረት አራሾቹ የምግብ ጥገኞች ስለሆኑ ምግቡን ወደ ገንዘብ መቀየር ስለተሳናቸው ነው።

የቤተሰብ ቅጥያ ቅንብር አስመልክቶ አንዳንድ ቤተሰብ ምርጫን አስመልክቶ ማዕቀብ እንደተደረገባቸው ቅሬታቸውን ገልጸዋል። ለምሳሌ በትግራይ ሕዝብ የንብ እርባታ አስመልክቶ ተጽእኖ እንደተደረገበት ገልጿል። አንዳንድ ቤተሰብን ሆን

ብለው እንዳስወገድዋቸው፣ ድሃ ቤተሰቦች ከፕሮግራሙ ተመንጥረው እንዲወጡ እና የአመራረጥ አድልዎ በሌሎች ቤተሰብ እንደሚደረግም የገለጹ አሉ።

በፈቃደኛነት የተመሰረተ የሰፈራ ፕሮግራም በጽንሰ-ሐሳብ ደረጃ መልካም ነው ቢባልም በፖሊሲና በመተግበር ደረጃ ግን አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። ፕሮግራሙ በቀና መንፈስ የታቀደና አስፈላጊ ቢሆንም ቅሉ የሰው ልጅ ባጠቃላይ ለቀዩ ልዩ ስነልቦናዊ ስሜት ስላለው በቀላሉ ወደ ሌላ ቦታ ማስፈር ቀላል አይሆንም። ስለሆነም ከፍተኛ የትምህርት ዘመቻ የሚጠይቅና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማስፈን ደግሞ ለስነልቦናዊ ትምህርት ቀዳሚነት እንዲሰጠው ያስፈልጋል። መንግሥት ግን ይኸንን ግንዛቤ ከማድረጉ በፊት 440,000 ቤተሰቦች ወይም 2.2 ሚልዮን ሕዝብ በሰፈራ ፕሮግራም እንዲሰማሩ ፕሮግራም አወጣ።

## IV. እርጅና እና ድህነት በኢትዮጵያ

ይህ ምዕራፍ አሰፋ ባለሂርና ፍሬሒወት ይርሳው ስለእርጅናና ድህነት በኦክተበር 2003 በ ዳርኤስሰላም፡ ታንዛንያ በተካሄደው የአከባቢ ሰሚናር ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ይወያያል። አሰፋ በኢትዮጵያ የሥራና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስተር የአረጋውያን ጉዳይ ቡድን መሪ ሲሆን ፍሬሒወት ደግሞ በፋይናንስና ምጣኔ ሃብታዊ ልማት የደኅንነት ተከታታይ ጓድ ልዩ አዋቂ ነች።

አሰፋና ፍሬሒወት እንደሚሉት ከሆነ “የደኅንነት ልዩ ልዩ ገጽታዎች በሰፊውና ጠለቅ ባለ መንገድ ለመረዳትና ድህነትን ለመቅረፍ የመንግሥቱ ማእከላዊ ፖሊሲ” ነው። የኢትዮጵያ የድህነት ትንተና መሰረት ያደረገው በቤተሰብ ገቢና የመብል ወጪ እንዲሁም የደኅንነት ቁጥጥር አሰሳ ሆኖ ዘገባውም የሚቀርበው በማእከላዊ የስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ነው። የደኅንነት ቁጥጥር አሰሳ በየዓመቱ የሚካሄድ ሆኖ የሚወክለውም የመስተዳድር ክልሎችን ነው። በ1999/00 ዓ.ም. የደኅንነት ቁጥጥር አሰሳ በ25,917 ቤተሰብ ላይ ሲካሄድ የቤተሰብ ገቢ መብልና ወጪ አሰሳ ደግሞ በ17,332 ቤተሰቦች ላይ ተካሂዷል። የአሰሳውም ጥናት ለመደገፍ ያህል ለ2003/2004 ዓ.ም. ‘የደኅንነት ተሳትፎነት ግምገማ’ የሚል ተጨማሪ ዘዴ ተፈጥሯል።

በ1999 ዓ.ም. በተደረገውም ጥናት መሰረት ደግሞ በኢትዮጵያ ፍጹም ድሃ ወይም ከድህነት በታች የሚኖሩ ሰዎች ከጠቅላላ የሕዝብ ብዛት 44 ከመቶ መሆናቸውን ታውቋል። የከተማና ገጠር ድህነት ሲነጻጸር ደግሞ በከተማ ድሃ የተባሉት ሰዎች 37 ከመቶ ሲሆኑ በገጠር ግን 45 ከመቶ ናቸው፣ ስለሆነም የገጠሩ ድህነት ከከተማው የበለጠ ነው።

እርጅና እና ድህነት የተቆራኙ ለመሆኑ ከጥናቱ ማወቅ ተችሏል፣ የእያንዳንዱ ቤተሰብ የልጆች መብዛትና የገቢ ምንጭ ውስንነት ለዚሁ ማሕበራዊ ችግር ዋና ምክንያት ሲሆን ትልቅ አደጋ የሚያጋጥማቸው ደግሞ አረጋውያን ናቸው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ አረጋውያን በኢትዮጵያ ልጆቻቸው በኤች አይ ቪ/አይድስ ከሞቱ የልጅ ልጆቻቸውን እንዲንከባከቡ ተጨማሪ ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል።

የኢትዮጵያ የቀጣይ ልማትና ድህነትን የመቅረፍ ስትራተጂ ከሞላ ጎደል የተባበሩት መንግሥታት የሚሌንየም የልማት ዓላማን የሚያንጸባርቅ ሆኖ በሚከተሉት ግቦችም ላይ ያተኰረ ነው፡-

- ከ1990 ዓ.ም. እስከ 2005 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በረሃብ ለሚሰቃዩት ሰዎች ቁጥር በግማሽ መቅረፍ
- ከ 1990-2015 ዓ.ም. ከአምስት ዕድሜ በታች የሞት ቁጥር በሁለት ሦስተኛ መቀነስ
- ከ1990-2015 ዓ.ም. የእናታዊ ሞት በሦስት አራተኛ መቀነስ
- በ2015 ወንዶችና ልጃገረዶች በኢትዮጵያ ሁሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ማገባደድ እንዳለባቸው ማረጋገጥ
- በ2005 ዓ.ም. የጾታ ማበላለጥ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲጠፉ፣ በማንኛውም የትምህርት ደረጃ ደግሞ 2015 ዓ.ም. ከመድረሱ በፊት የጾታ ማበላለጥ እንዲጠፋ
- በ2015 በቀጣይነት የሚጠጣ ንጹህ ውሃ የማያገኙ ሰዎች በግማሽ መቀነስ፣ የኤች አይ ቪ/አይድስ መስፋፋት በ2015 እንዲቀለበስ

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ግቦች፡ ምንም እንኳ የተባበሩት መንግሥታት የሚለንየም ዓላማዎችን የሚያሟሉ ቢመስሉም በስነ-ሐሳብም ሆነ በመተግባር ደረጃ ለሚያጋጥሙ ችግሮች በደንብ የታሰበበት አይመስልም። አሰፋና ፍሬሒወት ደግሞ የመንግሥት ሰራተኞች ስለሆኑ ነጻ በሆነ መንገድ ግቦችን መንቀፍ አልቻሉም እንጂ መጀመርያ መታየት የነበረበት ጉዳይ የጊዜ ገደቡ ነው፣ በተለይም ለድሃ የሦስተኛ ዓለም አገሮች የጊዜ ገደብ አያዋጣም፡ አይሰራምም። እጅግ የበለጸጉ አገሮች እንኳ አንዳንዴ የአምስት ዓመት ፕላን በግብር መተርጐም የማይችሉበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ የጾታ ማበላለጥ በ2005 ዓ.ም. ለማጥፋት የሚለው ግብ በኢትዮጵያ ስኬታማ አልሆነም። በተጨማሪም ሲ ራይት ሚልስ ያለውን ካስታወስን ስታቲስቲክስ ሐቅን ሊሸፍን ስለሚችል በግማሽ ወይም በሦስት አራተኛ መቀነስ የሚለውን ሐረግ ትርጉመ-ቢስ ሊሆን ይችላል።

እዚህ እኔ በነቀፌታ መልክ የማቀርበው ያለሁት በውጠኑ ላይ ያነጣጠረ ሳይሆን አንዳንድ ግቦች ከመጀመርያውኑ የተዛባ ጥናትን መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። ለዚህም ነው ስኬታማ ሊሆኑ ያልቻሉት። ለምሳሌ የኤች አይ ቪ እና አይድስ በኢትዮጵያ መስፋፋት የበሽተኛው ቁጥር በቅጡ የሚታወቅ አይደለም፣ የአይድስ ማሕበራዊ ችግርም ማሕበረሰቡ፣ በተለይም ሕመምተኛው፣ በግልጽ ባደባባይ አውጥቶ የሚናገርለት ጉዳይ አይደለም፣ ስለሆነም በይፋ ወጥተው ህክምና የሚፈልጉ በሽተኞች ቁጥራቸው አነስተኛ ነው። በዚህም ችግር ላይ የኤች አይ ቪ (ቫይረስ ወይም ሕዋስ) ፍልፈላ ወይም የሕመም ምልክት (incubation period) በቀላሉ ስለማይታወቅ (የደም ምርመራ ካልተደረገ በስተቀረ) በሽተኛው ራሱ መታመሙን ስለማያውቀው ሌሎች ብዙ ጤናማ ሰዎችን ሊበክል ይችላል። ለዚህ ችግርና ለሁሉም ከነገባቸው ለተጠቀሱት ማሕበራዊ ችግሮች ታድያ መፍትሔ የሚገኝባቸው ነጻ ጥናታዊ ጽሑፎች ሲቀርቡና በጽሑፎቹም መሰረት መንግሥት የጦፈ እርምጃ (መጠነ-ሰፊ የትምህርት ዘመቻም በማከል) ሲውስድ ብቻ ነው።

ሌላው በአሰፋና ፍሬሒወት የቀረበው ነጥብና አሳማኝ ሆኖ ያገኘሁት ግን የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ደኅንነት እና ማሕበራዊ ግልጋሎት ገና በእንጭጭነታቸው ነው የሚገኙት ሳሉት ነው። እነሱ እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ እስከ 1994 ሃገራዊ ማሕበራዊ ደኅንነት የሚባል አልነበረም። በ1996 ዓ.ም. ደግሞ ማሕበራዊ ደኅንነት የልማታዊ ማሕበራዊ ደኅንነት ፖሊሲ አካል መሆኑን ተቀበለ። የዚሁ ፖሊሲ ዋና ነጸብራቆች የሚከተሉት ናቸው፦

- ባስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ ህጻናትና ወጣቶች
- በከባድ የምጣኔ ሃብታዊና ማሕበራዊ ችግሮችን የሚሰቃዩ ሴቶች
- እንክብካቤና እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው አረጋውያን
- የአካል፡ የአንጎልና የስሜት ችግሮችን ያጋጠማቸው ሰዎች በተለይም አረጋውያን አስመልክቶ ፖሊሲው ስድስት ዓበይት የአማላጅ እርዳታዎችን አስቀምጧል
- የማሕበራዊ ችግሮች ሰለባ የሆኑትን ሰዎች
- ሕብረተሰቡ ከአረጋውያን የልምድ/ተመክሮ ሃብት ተጠቃሚ እንዲሆን፣ እነሱንም ከለውጥ ጋር አብረው እንዲራመዱ እርዳታ ማድረግ
- በሕብረተሰባችንና በባህላችን አወንታዊ የምንላቸውን ሁሉ ነገር እንዲጠናከሩና አስፈለጊውን ጥረት ማድረግና የአረጋውያን ጽኑነትና ደኅንነት ማረጋገጥ
- አረጋውያን ተገቢ የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት በማሕበረሰቦች ይደረግላቸው ዘንድ ዝግጅቶች ያደርጋሉ፣ ቅድምያ የሚሰጣቸው ግን ላረጁ ሴቶች፣ ለተዳከሙና መንቀሳቀስ ያቃታቸውና የተሳናቸው ሰዎች፣ እንዲሁም ለተፈናቃይ እና ቤተሰብ ለሌላቸው አረጋውያን

በጥናቱ እንደተመለከተው በ2001 የኢትዮጵያ የስታቲስቲክስ ረቂቅ (Ethiopian Statistical Abstract) ባቀረበው ዘገባ የአረጋውያን ቁጥር በዕድሜ ከተመደበ የሚከተለውን ጠቅላላ ድምር እናገኛለን፦

| ዕድሜ | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|
| 60-64 | 1,098.00 |
| 65-69 | 813.070 |
| 70-74 | 555.964 |
| 75+ | 583.730 |
| ጠቅላላ የአረጋውያን ድምር | 3,051.964 |

ነገር ግን አሰፋና ፍሬሒወት በጥናታዊ ጽሑፋቸው ያሳሰቡት ነገር ቢኖር አረጋውያንን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ያለው መረጃ እጅግ በጣም አነስተኛ መሆኑን ነው። በተገኘውም መረጃም ቢሆን ከአረጋውያኑ ምን ያህል ድሃ እንደሆኑ ማወቅ አልተቻለም።

‘ዕድሜ ረዳት አለምአቀፍ ኢትዮጵያ’ ወይም በእንግሊዝኛ ስሙ HelpAge

International Ethiopia የተባለው ድርጅት ባደረገው የሰባት የተሳታፊ ንድፍ ሰሚናር ሰዎች ምግብና የደኅንነት ዋስትና አስመልክቶ በመጥፎ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን አመልክቶ ነበር። በሰሚናሩ እውቅና የተሰጣቸው ሌሎች የአረጋውያን ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፦

- መጥፎ መጠለያዎች
- ቤት አልቦነት
- የጥገኞች ቁጥር
- ለሴቶች ዕድል አለመስጠት
- አሉታዊ አመለካከት
- ከልማታዊ መፍትሔ ይልቅ ድኅማ
- የመንግሥት የማሕበራዊ ደኅንነት ሥርዓት አለመኖር
- እንክብካቤነት አለመኖር

በኢትዮጵያ ብቸኛ የደኅንነት ዋስትና የጡረታ አበል ብቻ ነበር። ባለፉት መንግሥታት በመንግሥት መስርያ ቤት ያገለገሉ 496,000 ሰራተኞች የጥሮታ አበል መብት ነበራቸው። ያሁኑ መንግሥት የጡሮታ ዕድሜ 60 እንዲሆን በአዋጅ ስለወሰነ የጡሮታ አበል ተጠቃሚዎች ቁጥር ከፍ ብሏል። ነገር ግን መንግሥት የገቢ ምንጭ ውስንነት ስላለው ሌሎች አረጋውያን የጡረታ አበል መብት እንዲኖራቸው አልተደረገም።

የአረጋውያን ችግር ለመፍታት ያህል መንግሥት በእርጅና ዕድሜ የሚገኙና ጡረተኞች በማሕበር እንዲደራጁና ድምጻቸውን እንዲያሰሙ አበረታቷል። ስለሆነም ድህነት በስተርጅና ለመቀነስ፣ ለአረጋውያንና ጡረተኞች መብት መከራከር፣ ስልጠና ለመስጠት፣ ከአረጋውያንና ጡረተኞች ጋር ለሚሰሩ ድርጅቶች ችሎታቸው እንዲዳብር በማለት 'የኢትዮጵያ የአረጋውያን ጡረተኞች አገር-አቀፍ ማሕበር' ተቋቁሟል።

የአረጋውያን ማሕበር ከማቋቋም ባሻገር የስራና ማሕበራዊ ደኅንነት ሚኒስተር እርጅናን በተመለከተ ሃገር አቀፍ ድርጊት እንዲኖር በማለት የማድሪድ ንድፍ (Madrid Plan) ወደ አማርኛ እንዲተረጐም ወሰነ። ከዚሁ ከማድሪድ ንድፍ በተጨማሪ ኢትዮጵያ በ1982 በቭየና አውስትርያ በተደረገው 'የቪየና ዓለም አቀፍ የእርጅና ተግባራዊ እቅድ' ጉባኤ ከተሳተፉት የተባበሩት መንግሥታት አባላት አንዷ ነበረች። በቭየና ንድፍ መሰረት ደግሞ በ1999 ዓ.ም. የዓለም አቀፍ የአረጋውያን ቀን ተብሎ እንዲሰየም ተደርጓል። የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት (አሁን አፍሪቃ አንድነት) በበኩሉ የቭየና ንድፍ ለመደገፍ በደርባን ደቡብ አፍሪቃ ባደረገው ጉባኤ ላይ የእርጅና ፖሊሲና የተግባር ዕቅድ አውጥቷል። በዚሁም ጉባኤ ኢትዮጵያ ተሳትፋለች።

## V. ማሕበራዊ ችግሮችና ሕብረተሱታፊ ስትራተጂ

ይህ ምዕራፍ ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የመገናኛ ስትራተጂ በሚል ርእሰ-ነገር በአንተነህ መኩርያ ተስፋየ የቀረበውን መሰረት በማድረግ ልጃገረዶች

ለሚደርሰባቸው የግበረስጋ በደል ለማየት ይሞክራል። አንተነህ መኩርያ በባህርዳር ዩኒቨሪሲቲ የጋዜጠኛነትና መገነኛ ክፍለ-ትምህርት ፕሮፌሰር ነው። አንተነህ የተጠቀመው ዘዴ ባህላዊ የቡና ጊዜ እንደ አሳታፊ የመገናኛ ስትራተጂ አድርጎ ነው። ኢትዮጵያ የህጻናት እርዳታ (Children Aid Ethiopia — CHAD-ET ---) ባቀናበረውና ባጠናቀረው መረጃ መሰረት በማድረግና በትኩረተ-ስብስብ ውይይቶች (focus group discussion) ላይ በመንተራስ ማሕበራዊ ችግሮችን ለማጥናትና ለመፍታት ተመኩሯል።

በኢትዮጵያ ምልአተ ሕዝቡ የጋርዮሽ ማሕበረሰባዊ አመለካከት ስላለው ማሕበራዊ እምነቶችና ባህል-ነክ ተግባራት የመገናኛ ተሳትፎ ስትራተጂዎችን በማራመድ ደረጃ ትልቅ ሚና ሊጫወት ይችላል። ከነዚህም ስትራተጂዎች የተመረጠው አንዱ ባህላዊ የቡና ጊዜ ነው። የዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ ግን ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በቡና ጊዜ ሳይሆን በማርካቶ አከባቢ የግብረስጋ በደል የሚደርስባቸውን ህጻናት ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ማሕበራዊ ችግር ተስፋፍቶ የሚገኘው በአዲስ ከተማና በሌሎች ቆሻሻ ሰፈሮችና ድሃ ቤተሰብ ባሉበት አከባቢ ነው።

ጥናቱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ደግሞ ቻድ-ኢትዮጵያ (CHAD-ET) 18 ፈቃደኛ ሴቶች ከአዲስ አበባ የሴቶች ማሕበር በመምረጥ በማርካቶ ዙርያና በዘጠኝ ቀበሌዎች የቡና ጊዜ እንድያደራጁ አሰለጠንዋቸው። ከሰለጠኑት የአከባቢው ሴቶች ከልዩ ልዩ ብሔራት ማለትም ከአማራ፡ ኦሮሞ፡ ጉራጌ፡ ትግራይ፡ ዶርዜ ወዘተ የተመረጡ ሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፡ የፕሮተስታንት እና የእስላም ኃይማኖት ተከታዮችም ናቸው።

የጥናቱ ውጥን ወይም ፕሮጀክት ለሦስት ዓመት ያህል ተካሂዷል። የቡናው ጊዜ በሴቶች ላይ ያተኮረ ቢሆንም ክልዩ ልዩ ባህል፡ መደብ፡ ጾታና ዕድሜ የተካፈሉ ሰዎችም ወደውታል።

ማሕበራዊ መገናኛዎችን አስመልክቶ ሁለት ዓይነት በምሳሌነት የሚቀርቡ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) የስርጭት ዘዴ አርአያነት (difussion model) በሽቅብታ ወይም ሰያፍ፣ ከላይ ወደ ታች እና አንድ መንገድ መገናኛ ዘዴ ያለው ሆኖ፣ 2) የአሳታፊ ሞዴል በሁለት መንገድና በአግዳሚ መገናኛ የተመሰረተ ግኑኝነት ያለው ነው። የአሳታፊ ወይም የሱታፌ መገናኛ አስመልክቶ በአርአያነት የሚጠቀሰው የምሁሩ የብራዚል ተወላጅ ፓውሎ ፍሬሪ 'የጭቁኖች የትምህርት ስልት' (Pedagogy of the Oppressed) የሚል ስነሃሳብ በመጽሐፍ መልክ የወጣ ነው። ከዚሁ የፍሬሪ ስነ-ሃሳብ የተዛመዱ ሌሎች ምሳሌዎች እንደ የብዙሃን አርአያ (maultiplicty paradigm)፣ ሥልጣን የመስጠት ዘዴ (empowerment approach), ነጻ እድገት (autonomous development) እና ሕዝብ መሰረት ያደረገ ልማት የመሳሰሉም አሉ።

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸውን ምሳሌዎች ጥቅማቸው ለሕዝብ ተሳታፊነት ማገልገል ብቻ ሳይሆን ተሳታፊው ሕዝብም የመወሰን ሥልጣን እንዲኖረው ለማረጋገጥም ጭምር ነው፣ አለዛ ተሳታፊው ቡድን ዝቅተኛ ወይም የላላ ተሳትፎነት ነው የሚያሳየው።

በማርካቶ የተካሄደው የቡና ጊዜ ተሳትፎነት ከኢመደበኛ የመገናኛ ዘዴ መደበኛ ዘዴው ስላየለ ተሳታፊዎቹ እንደተጠበቀውና በባህላዊ የቡና ጊዜ እንደሚታየው ነጻ ጨዋታና መረጃ መለዋወጥን እምብዛም ማድረግ አልቻሉም። ስለሆነም የትኩረት ስብሰብ ውይይት እንደታሰበው ስኬታማ ሊሆን አልቻለም። ይኸም ሆኖ ግን የፕሮጀክቱ ተሳታፊዎች ብዙሃኑ ተመጣጣኝ ጊዜ በእኩልነት ለሁላችን አልተሰጠንም ከማለታቸውም በላይ በቡና ጊዜም ጥያቄዎች ለመጠየቅ ዕድል አልተሰጠንም ብለዋል። አወያዮቹ የንግግር ችሎታ ላላቸው ብቻ ነበር ዕድል የሰጡት ብለው ቅሬታቻውን የገለጹ ተሳታፊዎችም ነበሩ። በተጨማሪም አወያዮቹ ከሁለት መንገድ የመገናኛ ዘዴ ይልቅ የአንድ አቅጣጫ ዘዴን ስለተጠቀሙ ተሳታፊዎቹ ነጻ የመሳተፍ ሥልጣን ሊቀዳጁ አልቻሉም።

በተጨማሪም አወያዮቹ ራሳቸውን እንደ አመቻች አወያይ ሳይሆን እንደ አስተማሪ ስላዩ ትርጉም ያለውና አጥጋቢ የሕብረተሰቡታፌ ስትራተጂ ግንኙነት ማበርከት አልቻሉም፣ አወያዮቹ ተሳታፊዎቹን በተለያዩ መንገዶች፣ ጥያቄ በመጠየቅም ጭምር፣ የሚሳተፉበት መንገድ ከመቀየስ ይልቅ ዋና ተግባራቸው መረጃ ማስተላለፍ ብቻ ስለነበር የፕሮግራሙ ዓላማ ግቡን ሊመታ አልቻለም። ተሳታፊዎቹ ስለችግሩ ያላቸውን እውቀት ማቅረብ ስላልቻሉ መፍትሔዎችን መጠቆም አልተቻለም። በሌላ በኩል ግን አወያዮቹን ሙሉ በሙሉ መውቀስ አይቻልም፣ ምክንያቱም ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱ "በ CHAD-ET አስፈላጊውን ሥልጠና አልተሰጠንም" ብለዋል።

አንዳንድ የትኩረት ስብሰብ ሰዎች በግል ሲጠየቁ ግን ችግሩን በደንብ የገለጹ አሉ። ለምሳሌ አንዷ ተሳታፊ በሚከተለው መልክ አቅርበዋለች፡-

> በልጆች ላይ የሚደርሰው የግበረስጋ በደል ዋና ምክንያቱ ድህነትና ያኗኗር ዓይነት ናቸው። ቤቶቻችን የተሰሩት በቀላሉ ወደ ጎረቤት ቤቶች መግባት የሚቻልበት መንገድ ነው። አንዳንዶቻችን ኑሮቻችንን የምንመራው አልጋዎቻችንን በማከራየትና ከነልጆቻችን መሬት ላይ በመተኛት ነው። አልጋ የሚከራዩ ሰዎች ለመፈለግ ወደ ውጭ በምንወጣበት ጊዜ ልጆቻችን ብቻቸውን ትተናቸው ነው የምንሄደው፣ በዚህም ጊዜ ነው ልጆቻችን ከሚከራዩም ሆነ ከጎረቤት የግብረስጋ ጥቃት የሚደርስባቸው።

ሴቶቹ ባጣቃላይ በቡና ጊዜ እንዳቀረቡት የችግሩ መንስኤ ድህነትና የቤት ችግር ነው። የሚኖሩበት አከባቢም የወደቀ አከባቢ ስለሆነ ሌሎች ማሕበራዊ ችግሮች እንደ ቆሻሻነትና ስርቆት ለውይይቱ አስፈላጊና አግባቢነት እንዳላቸው የጠቀሱም አሉ።

በፕሮግራሙ የተሳተፉ ሴቶች አብዛኞቹ በማርካቶ የኑሮ ጫፍ ላይ የሚኖሩ ናቸው። አብዛኞቹ እናቶች ናቸው፣ ዕድሜአቸውም ከ25 እስከ 45 ነው፣ አብዛኞቹ በ30 ዕድሜ አከባቢ ላይ ናቸው፣ አብዛኞቹ የቤት እመቤቶች የነበሩና ኗሮአቸውን የሚገፉት ደግሞ ጠላና እንጀራ በመሸጥ ከሚያገኙት አነስተኛ የገቢ ምንጭ ነው።

ጥቂት ከመንግሥት መስርያ ቤት ባለሙያዎች ደግሞ ተሳትፎዋል። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በሂወት ማቆያ ነበር የሚኖሩት።

ብዙ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ሴቶች ደግሞ “ወንዶች በውይዩቱ መሳተፍ ነበረባቸው፣ ምክንያቱም ችግሩን መፍታት የሚቻለው በሴት ላይ በማትኮር ብቻ አይደለም፣ ወንዶች ናቸው ልጆቻችንን በግብረስጋነት የሚበድሉት” ብለዋል። አንዳንድ ሴቶች ግን ከባሎቻቸው ጋር በፕሮግራሙ መሳተፍ እንደማይፈልጉ የገለጹም አሉ።

ይህ የሕብረተሱታፌ ስትራተጂ እንደተጠበቀው ስኬታማ ባይሆንም ሌላ ፕሮግራሞች ግን የቡና ጊዜው በር ከፍተዋል ማለት ይቻላል። በምዕራፍ I ሠ ‘እናታዊ ሞት በኢትዮጵያ’ (ገጽ 13) እንደተጠቀሰው የጤና ትምህርትን አስመልክቶ የቡና ጊዜ ብዙ ጥቅም እንዳለው ለማወቅ ተችሏል።

## VI. የኢትዮጵያ ስደተኞች ማሕበረሰብ

ከደርግ አገዛዝ ጊዜ ጀምሮ በሚልዮኖች የሞቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ከሃገራቸው ተገደው በመውጣት ወደ ልዩ ልዩ አህጉሮች ተሰደዋል። ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የሌሉበት አገር አለ ማለት አይቻልም፣ በአፍሪቃ አገሮች እንደ ከንያ፡ ደቡብ አፍሪቃ፡ ሱዳን የመሳሰሉ፣ በአውሮጳ ጠቅላላ፣ በሰሜን አመሪካ (ዩናይትድ ስተይትስ እና ካናዳ)፣ በመካከለኛው ምስራቅ፣ እንዲሁም በአውስትራልያ። ቁጥራቸውም አነስተኛ ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በደቡብ አመሪካና በካሪብያን አገሮችም አሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ ማለትም ባለፉት ሁለት አሰርት ዓመታት ደግሞ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ዓረብ አገሮች የተጓዙ ስደተኞች የዓረብ አረሜኔነት ሰለባ የሆኑትን የዓለም ሕዝብ የታዘበው ጉዳይ ነው። እነዚህ በሕገወጥ መንገድ የወጡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ወደ አገራቸው እየተመለሱ ናቸው፣ ቁጥራቸውም ወደ 50,000 እንደሆነ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ገልጿል። ‘የአረብ ዜና’ (Arab News) የሚባል ድረ ገጽ እንደዘገበው ከሆነ ግን በ 2013 ዓ.ም. ብቻ 38,827 ኢትዮጵያውያን በየመን በኩል ወደ ሳውዲ አረብያ እንደገቡ ነው።

በዓለም ጠቅላላ የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ቁጥር ለማወቅ ቢያስቸግርም ቀጥሎ እንደተመለከተው በሃገሮችና በአህጉሮች ያሉት የስደተኞች ቆጠራ ለማቅረብ ተመኩሯል።

የአመሪካ የሕዝብ ቆጠራ ጽሕፈት ቤት (US Census Bureau) በ 2000 ዓ.ም. እንዳቀረበው ከሆነ በጠቅላላ 86,918 ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የዩናይትድ ስተይትስ ክፍላተ-ሃገራት እነደሚኖሩ ሲገመት በዋሽንግተን ዲሲ እና ዙርያ ብቻ ግን 250,000 ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ነው የሚነገረው። ከ2007 እስከ 2011 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ቁጥር በአመሪካ ወደ 151,515 ከፍ ብለዋል። አሮን ማትዮ ታራስ እንዳጠናከረው ከሆነ ግን በኢትዮጵያ የተወለዱና በአመሪካ የተወለዱት ኢትዮጵያውያን ከተደመረ 460,000 ይደርሳል፣ ከነዚሁ 350,000 በዋሺንግተን ዲሲ፣ 96,000 በሎስ አንጀልስ፣ 10,000 በኒው ዮርክ፣ 30,000 በዳለስ-

ፎርትዎርዝ እንደሚኖሩ ታውቋል። በካናዳ 15,725 ኢትዮጵያውያን ይኖራሉ፣ በርካቶቹ በቶሮንቶና ኦታዋ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ በተለያዩ የካናዳ ግዛቶች ብርትሽ ኮለምብያ ጭምር ይኖራሉ።

በአውሮጳ በየሃገሩ የኢትዮጵያ ስደተኞች ቢኖሩም በርካታው ግን በጣልያን፡ በእንግሊዝ፡ በጀርመን፡ በሆላንድ እና በስካንዲናቭያ ነው የሚኖሩት። በእንግሊዝ 20,000 በጣልያን ደግሞ 30,000 ኢትዮጵያውያን ስደተኞች እንዳሉ ታውቋል።

በመካከላኛው ምስራቅ በሱዑዲና በገልፍ አገሮች ምን ያህል ኢትዮጵያውያን እንዳሉ አይታወቅም፣ በጁላይ 2013 የሕዝብ ቆጠራ እንደዘገበው ግን በሱዑዲ አረብያ 90,000 በሊባኖስ ደግሞ 30,000 ኢትዮጵያውያን ስደተኞች እንዳሉ ታውቋል። በእስራኤል ግን በየጊዜው በቀረበው የሕዝብ ቆጠራ አማካኝነት ከ90,000 በላይ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ታውቋል። ወደ እስራኤል የተጓዙት ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ ቤተ-እስራኤል ወይም ፈላሻ ሲሆኑ ቁጥራቸው አነስተኛ ክርስትያኖችም አሉ። ገና እስራኤል በ1948 ዓ.ም ስትቋቋም የሄዱ ፈላሻዎች ቢኖሩም በገፍ የሄዱት ግን ከ1985 እስከ 2013 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነው። በ1985 ዓ.ም. በ 'ሙሴ ዘመቻ' 7500 እና በ 'ጃሹዋ ዘመቻ' 550፣ በ1991 በ 'ሰለሞን ዘመቻ' 14,300 ቤተ-እስራኤሎች ወደ እስራኤል ገብቷል። በተጨማሪም ከ1991 እስከ 1999 ዓ.ም. 11,511 እና ከ1998-2013 ዓ.ም. 32,000 ፈላሻዎች ወደ እስራኤል ሲገቡ በቅርቡ ደግሞ 2,173 ከቋራ፡ ጎንደር ወደ እስራኤል ተጉዟል። ጠቅላላ ወደ እስራኤል የሄዱ ፈላሻዎች 91,825 ነው። ነገር ግን እነዚህ ስደተኞች ባሁኑ ጊዜ ትውልደ-ኢትዮጵያ እንጂ ኢትዮጵያውያን ናቸው ማለት ያዳግታል። በርካታው ቤተ-እሰራኤሎች በእስራኤል ቆይታቸው ደስተኞች አይደሉም፣ የነጭ ዘረኝነት ያጠቃቸዋል፣ ሴቶቹም እንዳይወልዱና መካን ሆነው እንዲቀሩ የጽንስ መከላከያ መርፌ እንደተወጉ የእስራኤል መንግሥት በጃንዋሪ 2013 ዓ.ም. በይፋ ያመነበት ጉዳይ ነው። በጁላይ 2013 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ እንደሚያመለክተው ከሆነ ደግሞ ባሁኑ ጊዜ ፈላሻና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ተደምረው በእስራኤል የሚኖሩት ስደተኞች 130,000 ደርሷል።

የኢትዮጵያ ስደተኞች ማሕበረሰብ በሰሜን አመሪካ አጠቃላይ ሁኔታ ሲገመገም አብዛኞቹ በደህና ኑሮ የሚኖሩ ናቸው፣ በርከት ያሉ ደግሞ የራሳቸውን ተቋመ-ንብረት የሚመሩ ናቸው። በዋሽንግተን ዲሲ ኢትዮጵያውያን በሁሉም ዓይነት ስራዎችና ንግዶች ተሰማርቷል ማለት ይቻላል፦ ከታክሲ ነጂነት እስከ እንጀራ ሻጪነት፣ ከአነስተኛ ክዮስክ እስከ ሬስቶራንት፡ ቡና ቤቶችና ትላልቅ ሱቆች ንብረትነት እና የመኪና ማቆምያ ቤቶች አስተዳዳሪነት። በርካታ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ደግሞ በልዩ ልዩ ሞያዎች እንደ የሕግ ጠበቃነት፡ ጋዜጠኛነት፡ አስተማሪነት፡ የመንግሥት መስርያ ቤት ጸሐፊነት፡ የጥርስ ሃኪምነት፡ በሆስፒታልና ጤና ጣብያዎች ሃኪምነትና ነርስነት (አስታማሚነት)፡ እንዲሁም በማሕበራዊ ደኅንነት አማካሪነት የተሰማሩም አሉ። ሌሎች ኢትዮጵያውያን በተመሳሳይ የስራ መስኮች የተሰማሩ በትላልቅ ከተሞች እንደ ኒው ዮርክ፡ ቦስተን፡ አትላንታ፡ ዳለስ፡ ኮለምበሰ ኦሃዮ፡ ደንቨር፡ ሎስ አንጀልስ፡ ኦክላንድ ካሊፎርንያ፡ ሲያትል፡ ቶሮንቶ፡ ኦታዋ ወዘተ ይኖራሉ።

በአወሮጳ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በኑሮአቸው ከአመሪካ ካሉት ስደተኞች በብዙ ረገድ ቢመሳሰልም እንደ አመሪካ ውስጥ ካሉት ስደተኞች በርካታ የንብረተ-ተቋም የንብረትነት ዕድል ሊያጋጥማቸው አልቻለም፣ ምክንያቱም በአውሮጳ ያለው ጸጋ ከአመሪካ ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም አነስተኛና ውሱን ነው። ግን በአውሮጳ ያሉት ኢትዮጵያውያን የሚያገኟቸው ማሕበራዊ ግልጋሎት እንደ ነጻ ሕክምናና ነጻ ትምህርት በአመሪካ ያሉት ስደተኞች ሊጎናጸፉ አልቻሉም፣ ምክንያቱም በአውሮጳ የማሕበረ-ዴሞክራሲ ስርዓት በሰፊው የተዘረጋና ስር የሰደደ ሲሆን በአመሪካ (ዩናይትድ ስተይትስ) ግን ከናካቴው የለም።

በመካከለኛው ምስራቅ በልዩ ልዩ የዓረብ አገሮች የተሰደዱ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነ በሞያዊ ስራዎችና ንግድ የተሰማሩ ሲሆኑ ብዙዎቹ ግን - በተለይም ሴቶች - በግርድና ወይም የቤት ስራ የተሰማሩ ናቸው። እነዚህ በነዳጅ የበለጸጉ የዓረብ አገሮች ባሁኑ ጊዜ ልዩ ልዩ የአውሮጳ፡ የአመሪካና፡ የጃፓን ተክኖሎጂ በማስገባት የሚያሸበርቁ ከተሞች ቢሰሩም ከኋላ ቀር በህላቸው ግን መላቀቅ አልቻሉም። ስለሆነም በሴቶች፡ በልጆችና ስደተኞች ላይ ብዙ ግፍ ይሰራሉ። በቅርቡ በሳውዲ አረብያ በኢትዮጵያውን የደረሰው አሰቃቂ ግፍም የዚሁ ኋላ ቀር ባህል ነጸብራቅ ነው። እነዚህ የዓረብ ሰለባ የሆኑትን ወገኖች ግን በትውልድ አገራቸው ባለው ድህነትና በህገ-ወጥ ዝውውር ደላሎች ገና ለገና ፍዳቸውን አይተው ነበር ወደ ስደት ያመሩት። አብዛኞቹ የሕገ-ወጥ ስደተኞች ኢትዮጵያውያን ቀደም ብሎ ከወሎና መሃል ኢትዮጵያ አከባቢ፣ ቀጥሎ ደግሞ ከደቡብ ኢትዮጵያና አጓራባች ክልሎች እንደ ኦሮምያና ሃረር ኣከባቢ ነበር ለዓረብ ስራ የተመለመሉት፣ በርካቶቹ ደግሞ ከገጠር ኢትዮጵያ የተጓዙ ስለሆኑ የቋንቋና የባህል ድንጋጤ (culture shock) አጋጥሟቸዋል።

በ2000 እና 2001 ዓ.ም. በተለያየ መልክ ከአገራቸው ተፈናቅላው ወደ ከንያና ሶማልያ ተጉዘው የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ደግሞ በ2006-07 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ክፍተኛ ኮሚሽነር በጠየቀው መሰረት አውስትራልያ አስተናጋጅ ሆናለች።

የአውስትራልያ የስደተኞች ኅብረ-ባህል ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ባዘጋጀው ስለ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ማሕበረሰብ ዘገባ እንደሚያመለክተው በ2001 ዓ.ም. 3,600 ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለዱት ኢትዮጵያውያን አውስትራልያ ውስጥ ይኖሩ ነበር። አብዛኞቹ በቪክቶርያ ክፍለ-ሃገር ሲኖሩ 60 ከመቶ ከነዚሁ ደግሞ የእንግለዚኛ ቋንቋ ችሎታቸው በጣም ደካማ ነበር፣ 42 ከመቶ ያላገቡ ሲሆኑ 33 ከመቶ ደግሞ ሁለት ሰው የያዘ ቤተሰብ ሆነው ነበር የገቡት፣ 3 ከመቶ የሰባት ወይም ከሰባት በላይ ሰው የያዘ ቤተሰብ ሆነው ነበር የተጓዙት።

በ2000-05 ዓ.ም. ወደ አውሰትራልያ የተጓዙት ኢትዮጵያውያን የዕድሜ ክልል በከፊሉ ለመጥቀስ ያህል 430 ከስድስት ዓመት ዕድሜ በታች፣ 155 ከ16-17 ዕድሜ፣ 943 ከ25-34 እና 13 ከ65 ዕድሜ በላይ ናቸው። በጎሳ አከፋፈል ከታየ ደግሞ ትግርኛ ተናጋሪዎች 7 ከመቶ፣ አማርኛ ተናጋሪዎች 14 ከመቶ፣ ኦሮሞ ተናጋሪዎች 16 ከመቶ ሲሆኑ ሌሎች ብሔራቸው ወይም ጎሳቸውን ያልተገለጸው ደግሞ 59 ከመቶ ናቸው።

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ከሱዳን ወደ አውስትራልያ የተጓዙ ሲኖሩ በ2004 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ አብራከም ከተባለው የሱዳን መጠለያ 350 ኢትዮጵያውያን በአውስትራልያ እንዲሰፍሩ ተደርጓል። እነዚህ ስደተኞች በመጠለያው ለብዙ ዓመታት ስለተቀመጡ (አንዳንዱ እስከ 20 ዓመት በመጠለያው የቆዩ አሉ) ልጆቻቸውም እዛው መጠለያ የተወለዱ አሉ። ከነዚህ ከአብራከም ወደ አውስትራልያ የሄዱት ስደተኞች አብዛኞቹ በእናት የሚመሩ ቤተሰብ ሲሆኑ ብዙዎቹ ደግሞ ክርስትያን ሆነው የብሔር መንነታቸው ደግሞ አማራና ትግራይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ አውስትራልያ የገቡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች 700 ሲሆኑ አብዛኞቹ የትምህርት ደረጃቸው ከ 3-4 ዓመት ብቻ የትምህርት ክትትል ያደረጉ ናቸው። ጤንነታቸው በተመለከተም አንዳንዱ የሳምባ ነቀርሳ በሽታ ሲያጠቃቸው ሌሎቹ ደግሞ ኤች አይ ቪ፣ የጉበት ብግነት፣ የስኳር በሽታ፣ የደም ግፊትና ደካማ የዓይን ብርሃን በሽታዎች የተጠናወተባቸው ናቸው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በኢትዮጵያ ውስጥ በጠፈ መልኩ መዋእለ ንዋያቸውን ስራ ላይ እያወሉ ናቸው፣ በርካታ የንግድ መናሃርያዎች ወይ በወኪልነት ወይም ደግሞ በአካል በመጓዝ የከፈቱም አሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ስደት አላቋረጠም፣ በላፉት 12 ዓመታት ብዙ ኢትዮጵያውያን በ ዲቪ ቪዛ አማካኝነት ከኢትዮጵያ በቀጥታ ወደ አመሪካ የገቡ አሉ፣ ከነዚህ አንዳንዱ ደህና የገቢ ምንጭ ወይም የንግድ ሥራ የነበራቸው ሲሆኑ በአመሪካ አሸብራቂ አምሳልነት ተታለው የመጡ ሲሆኑ፣ አመሪካ እንደጠበቁት ሆኖ ሳያገኙት ሲቀሩ ደግሞ ወደ ትውልድ አገራቸው የተመለሱ አሉ።

## VII. አዳዲስ የፈለቁ ማሕበራዊ ገጽታዎች

በደርግ አገዛዝ ጊዜና ባሁኑ የሕአዴግ ጊዜ በኢትዮጵያ አያሌ አወንታዊና አሉታዊ ማሕበራዊ ገጽታዎች ተከስተዋል። እነዚህ ገጽታዎች የተወሳሰቡ ቢሆንም ቅሉ ከሞላ ጎደል በሁለቱ የፖለቲካ ሥርዓቶች ጫና የተፈጠሩ ናቸው ማለት ይቻላል። አንዳንድ ጊዜ ያልተጠበቀ የታሪክ ዱብ ዕዳ ስለሚኖር በአስተሳሰብ ይሁን በአኗኗር ዘዴ ሕዝቡ በተለያየ መንገድ ከውስጥ ከሚፈልቁና ከውጭ ከሚገቡትን ባህሎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሊያንጸባርቃቸው ይችላል።

በደርግ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተጨቆነበት፡ የተጐሳቀለበትና የተዋረደበት ጊዜ ነበር ማለቱ የተጋነነ አይሆንም፣ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተደርጎ የማይታወቅ መንግሥት በሕዝቡ ላይ የሞትን አዋጅ (ቀይ ሽብር) በማወጅ የኢትዮጵያ ከተሞችን ወደ ትላልቅ እስር ቤቶችና የሰው ቄራዎች ቀይሯቸው ነበር። የሞት አዋጁ በተለይ በወጣቱና በምሁሩ ላይ ያነጣጠረ ስለነበር ኢትዮጵያን ሊመሩዋት ይችሉ የነበሩትን እልፍ አእላፍ ዜጎች ባክነው ቀርተዋል። ነገር ግን በእንዲህ ያለ በደም የጨቀየ ሥርዓት አወንታዊ ነገሮች ነበሩ ማለት አዳጋች ቢመስልም፣ በጨለማ ከወክብት እንደሚታዩ ሁሉ፣ በደርግ ጊዜም ጠቃሚ ማሕበራዊ

ገጽታዎች ተከስተው ነበር። ለምሳሌ በደርግ ጊዜ በመጠኑም ቢሆን በኢትዮጵያውያን ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥ ተከስቷል፣ የፊውዳሉ ሥርዓት ከተገረሰሰ በኋላ አንጻራዊ በሆነ መንገድ ሕዝቡ ልዩ ዝንባሌዎችን ማሳየት ጀምሮ ነበር። የመሬት አዋጁ ራሱ በአራሹ ዘንድ የንብረት ባለቤትነት ስሜት ብቻ ሳይሆን መተማመንና የመወሰን መቻል አስተሳሰብም ሰርጸ ነበር። ከመሬት አዋጁ ባሻገር ደርግ የኪነት ስነምግባር በማበረታታት በሰፊው ስለተያያዘው ድሮ አዝማሪ ወይም አዝማሪነት በአሉታዊነት ይታይ የነበረው በደርግ ጊዜ ሰዉ ሁሉ አዝማሪ መሆን የፈለገ ነበር የሚመስለው። ስለሆነም በደርግ ጊዜ የድምጽ ተዋንያን እንደ አሸን ፈለፈሉ፣ በዛውም መጠን በዘፈን፡ በዳንስ እና ድራማ ጥበበኝነት በለጸጉ፣ እስከ አሁን ድረስም እየቀጠለ ነው ያለው።

ሌላ በደርግ ጊዜ የተፈጠረ አወንታዊ ገጽታ መሃይምነትን ለማጥፋት በተደረገው የጠፈ ዘመቻ ነው። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ማንበብና መጻፍ ችለው ነበር። ነገር ግን በደረግ ጊዜ መደበኛ ትምህርት አይውደቅ አወዳደቅ ነበር የወደቀው። ብቃት ያላቸው የመምህራን እጥረት፣ የትምህርት ቤቶች በተማሪ ብዛት መጨናነቅ፣ በሁለት ወይም ሦስት መቀያየር ተማሪን ማስተናገድ፣ የትምህርት ዓይነት (ብቃት) መዝቀጥ ወዘተ መደበኛ ትምህርቱን ክፉኛ ጎድተውታል። በዚሁ ችግር ላይ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃው በቀይ ሽብር ስለተበከለ የተማሪ የመማር ፍላጎት በዛው መጠን አዘቀጠ። ከዚሁ አሉታዊ ማሕበራዊ ገጽታ ለማምለጥ ደግሞ ወጣቱ ኢትዮጵያዊ በጎ ነው ከተባለ ኃይማኖቱን ቀየረ፣ መጥፎ ከተባለ ደግሞ ወደ እጸ-ፋርስነትና የአልክሆል መጠጥ ባህሎችን አዘነበለ። በዚህ ጊዜ ነበር ባጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ወጣቶች የጴንጠ ኃይማኖት ተከታዮች የሆኑት፣ በሥልጣን ላይ የነበሩና የመንግሥት ሰራተኞች ደግሞ ሙሱናን በሰፊው የተያያዙት።

በኢሕአዴግ ጊዜ የቀይ ሽብር ዓይነት ፍርሃት በሕዝቡ ዘንድ ባይኖርም የዴሞክራሲ ስርዓት ግን እንደተጠበቀው ሥር መስደድ ስላልቻለ ጋዜጠኞች ወይም ተቃዋሚ ስብስቦች ሃሳባቸውን እንደፈለጉና ሳይሰጉ መግለጽ አልቻሉም፣ ደፍረው ተቃውሞአቸውን ካሰሙ ደግሞ የእስራት ወይም የግዞት ሰለባ ነው የሚሆኑት። በተጨማሪም ኢሕአዴግ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ በ2005 እና በ2010 እርምጃ ስለወሰደ የተጎዱና የታሰሩ ወገኖች አሉ። ይህ የኢሕአዴግ አሉታዊ ገጽታው ሆኖ በርካታ አወንታዊ ገጽታዎች ግን አሉት። ከነዚህ ካስመዘገባቸው አወንታዊ ገጾች አንዱ የብሔሮች እኩልነት ነው፣ ተረስተው የነበሩ ብሔሮች ድምጻቸውን ማሰማት ጀመሩ፣ አብረው በአንድነት የግል እና የጋራ (ብሔራዊ እና ሃገራዊ) ማንነታቸውን ማክበር ጀመሩ። መጀመርያ ክልሎች እንደተፈጠሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሃገሪቷ አንድነት ሊያናጋ ይችላል የሚል ስጋት ደርሶባቸው ነበር፣ ይኸም ከአፍሪቃ የጎሳ ፖለቲካ አንጻር ሲታይ ተገቢ ስጋት ነው። በኢትዮጵያ ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ግን ሕዝቡ ከፖለቲካ ሥርዓቱና ከጎሳ ፖለቲካ በላይ በመሄድ ብዙ ጊዜ ለአንድነቱ ቆሟል። አሁን ወደ ኤሚል ዱርካይም ማሕበራዊ ስነ-ሐሳብ መለስ ብለን የጠየቀውን ጥያቄ (ገጽ 4 በዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍ) መመለስ እንችላለን። ዱርካይም "ሕብረተሰቦች ኅብረ-ባህል ወይም ኅብረ-ብሔር ሆነው የጠነከረ አንድነትን መጕናጸፍ ይችላሉ ወይ?" ብሎ ላቀረበው ጥያቄ አሁን በኢትዮጵያ ከተከሰተው የብሔሮች ሁናቴ ካገናዘብነው መልሱ 'አዎ' ነው የሚሆነው።

ከብሔሮች እኩልነት ባሻገር በኢሕአዴግ ጊዜ ከሰላሳ በላይ የኑቨሪሲቲዎች ተፈጥረዋል፣ ብዙ መንገዶችና ድልድዮች በከተሞችና በገጠር ተዘርግተዋል፣ የኤለትሪክ ኃይል በገጠር እንዲሰራጭ ተደርጓል፣ የሐዲድ መስመሮች በአዲስ አበባ እንዲሁም በሃገር ደረጃ እየተዘረጉ ናቸው፣ የመስኖ አጠቃቀም ከመቸውም ጊዜ በጠቅላላ ኢትዮጵያ እውን ሆነዋል። ከተሞቹ፣ በተለይም አዲስ አበባ፥ አዳማ፥ ሐዋሳ፥ ባህር ዳር፥ መቀሌ ወዘተ እጅግ በጣም ተቀይረዋል።

ባጠቃላይ በኢሕአዴግ ጊዜ ልማትን አስመልክቶ፣ ከአንዳንድ የተሳሳቱ ምጣኔሃብታዊ ፖሊሲዎች በስተቀረ፣ ትክክለኛ አቅጣጫ የያዘ ይመስላል። ነገር ግን ያልነበሩ ወንጀሎች በትላልቅ ከተሞች ደግሞ ተከስተዋል፣ የቤት ጉርጎራ፣ የመንገድና የንግድ ቤት ስርቆት በከፍተኛ ደረጃ ነው የሚካሄደው፣ ቅትለተ-ነብስም በዛው መጠን። ለምሳሌ በመቀሌ ሌቦች ጨለማን ተገን በማድረግ ብቻቸውን ለሚራመዱ ሴቶች ይከታተሏቸውና በድንጋይ ከመቷቻው በኋላ ቦርሳቸውን ነጥቀው ይሄዳሉ። በሌሎች ከተሞችም ተመሳሳይ ወንጀሎች ይካሄዳሉ።

በደርግ ጊዜ የሰፋውን ሙስና በሕአዴግ ጊዜ ብሶበታል፣ በደርግ ጊዜ የተፈጠሩትን እንደ ጴንጠ የመሳሰሉት አዳዲሰ ኃይማኖቶች ደግሞ በኢሕአዴግ ጊዜ በይበልጥ ተስፋፍቷል። በደርግ ጊዜ ያልነበራውን ግን አሁን እንደ ፋሽን የተያዘው ደግሞ የእስልምና አክራሪነት ነው። የእስልምና ኃይማኖት ኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት የነበረ ኃይማኖት ነው። የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ አካልም ስለሆነ እስላሙም ክርስትያኑም አብረው ለብዙ ዘመን ጎን ለጎን ኖረዋል። ይህ ችግር አይደለም። የአክራሪው የወሃቢና ሰላፊ ተካታዮች ግን በበጎ መንፈስ የተነሱ ስላልሆኑ የኋላ ኋላ በኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች ጉዳት ማድረሳቸው አይቀርም።

ሌላው በደርግ ጊዜ የጀመረውና በኢሕአዴግ የቀጠለው ማሕበራዊ ችግር እኔም ‘መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች’ በተሰኘው መጽሐፌ ውስጥ የተወያየሁበት የግብረገብነት ባህል መዳከም ነው። ባሁኑ ጊዜ ብዙ ሰው ክግብረገብነት ርቆ በቁሳዊ ባህል ስለተዘፈቀ ቋንቋው ሁሉ ገንዘብ ሆኗል፣ ያሁኑ ጋብቻዎች ለምሳሌ በፍቅር ሳይሆን በገንዘብ ላይ የተመሰረቱ ስለሆኑ ግራም ነፈሰ ቀኝ መፍረሳቸው አይቀርም። ይኸንን ችግር አስመልክቶ ከላይ በጠቀስኩት መጽሓፌ ‘ጋብቻና ሐላፊነት’ በሚል ርእስ ለውይይት አቅርቤዋለሁ። በዚሁ ጥናታዊ ጽሑፍም በምዕራፍ አንድ ፍችና መንስኤውን አይተናል፣ ችግሩን ከሚያባብሱት ነገሮች አንዱ ገንዘብ ነው። ይህ ግን መጠነኛ ማሕበራዊ ችግር ነው፣ ሌላ በጣም የሚያስፈራ በደርግ የጀመረውና በኢሕአዴግ የሚቀጥለው ያለ አዲስ አሉታዊ ባህል የሬሳ ሳጥን ስርቆት ነው። የቀብር ስነ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ጨለማን ተገን በማድረግ ሳጥኑን የሚሰርቁ ሌቦች አሉ። አቤት አቤት የሚያሰኝ ነው! አንድ ሌላ በኢሕአዴግ ጊዜ የተከሰተውን አዲስ አሉታዊ ማሕበራዊ ችግር የሕገ ወጥ የሰው ዝውውር ነው። የኢትዮጵያ ረድዮና ተለቪዥንን እንደለገለጸው በሕጋዊ መንገድ ሰውን የሚያዘዋውሩ ወኪል ድርጅቶች 400 ሲሆኑ ከነዚሁ 6 ከመቶ ብቻ ናቸው በሐቅነት የሚሰሩት። ኢሕጋዊ የሰው ዝውውር በተዘዋዋሪ መንገድ ሰዑዲ አረብያ ውስጥ በኢትዮጵያውያን ለደረሰው ግፍ አስተዋጽኦ አለው። ከዚህም በላይ የእንስሳት ኢሕጋዊ ዝውውር አስቸጋሪ ሆኖ ስለተገኘ ችግሩን ለመቆጣጠር በኦክተበር 29

2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አቋቊሟል። በኢህጋዊ የሰው ዝውውር ላይ ደግሞ እገዳ ተደርጓል።

በኢሕአዴግ ጊዜ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ አንዳንድ አወንታዊ ባህልና ትምህርተ-ነክ ነገሮችን ተፈጥረዋል። ለምሳሌ የብሔሮች ቀን በየዓመቱ በተለያዩ ከተሞች ይከበራል፣ የዛሬ ሁለት ዓመት በመቀሌ ተከብሯል፣ ዓምና በባሕር ዳር፣ ዘንድሮ ደግሞ በጅጅጋ ሱማሌ ክልል ውስጥ ይከበራል። የብሔሮች ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአካል ተገናኝቶ የሚተዋወቅበትና ተመክሮ የሚቀያየርበትን በዓል ነው። በተመሳሳይ መልኩ 'የከተሞች ሳምንት' የሚባል በዓል ደግሞ ላለፉት አምስት ዓመታት ሲካሄድ ቆይቷል። የአምስተኛው የከተሞች ሳምንት በባሕር ዳር በ ኖቬምበር 26 2013 ዓ.ም. ተጠናቋል። በበዓሉም 186 ከተሞች ተሳትፏል። የከተሞች ሳምንት ዋና ዓላማ ተመክሮዎች ለመቀያር ሆኖ ማሕበራዊ ችግሮችን (ለምሳሌ ስራ አጥነት) እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ ከተሞቹ ይወያዩበታል። በተጨማሪም ስለ ከተማ መስተዳድር፣ ስለ ንብረተ-ተቋም አያያዝ እና ስለ መዋእለ-ንዋይ አጠቃቃም ሐሳብ ለሐሳብ ይቀያየራሉ። የስድስተኛው የከተሞች ሳምንት ድሬዳዋ እንደትሆን ተመርጣለች።

ስለዚህ ባጠቃላይ ጎጂና ገንቢ ገጽታዎች በኢትዮጵያ ተከስቷል ማለት ይቻላል። ለወደፊቱ ደግሞ የትኛው እንደሚያመዝን ጥናት በማድረግ አሉታዊ ገጽታዎችን ቀስ በቀስ በማጥፋትና አዎንታዎቹን በማበልጸግ ለመጪው ትውልድ መንገድ መቀየስ ይበጃል። ማንኛውም ሕብረተሰብ ጠርቶ ሊጠራ አይችልም፣ አንጻራዊ በሆነ መንገድ ግን በጎ ገጽታዎችን የበላይነት እንዲኖራቸው ዜጎች ባጠቃለይ፣ ምሁራንና የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይ ደግሞ ታሪካዊ ሐላፊነት መሸከም አለባቸው።

## VIII. ማጠቃለያ

ከፍ ብለን የተወያየንባቸው ዓበይት ማሕበረዊ ጉዳዮች በሰባት ምዕራፎች ለማካታት ብንሞክርም ቅሉ በየወቅቱ አዳዲስ ሕበረተሰባዊ ወይም በህላዊ ክስተቶች ሊታዩ ስለሚችሉ በየጊዜው ጥገና ለማድረግ ከመሯሯጥ ገና ለገና ወይም በቅድምያ ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም መፍትሔ ለመፍጠር የሚቻልበት ሁኔታ መዘጋጀት አለበት። አንድ መንግሥት በየጊዜው ለሚፈጠሩ ማሕበራዊ ችግሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ አስቀድሞ መተንበይ መቻል አለበት፣ በዛውም መጠን መፍትሔዎቹን ማዘጋጀት አለበት። አለዛ ችግሮቹ ድንገት ደራሽ ከተደቀኑ መፍትሔ ለማግኘት ቢሯሯጥ የነ ተሎ ተሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ ነው የሚሆነው፣ አንድ ቤት በእሳት ከጋየ በኋላ እሳቱን ለማጥፋት መጣደፍ ከንቱ ሙከራ ነው የሚሆነው። መሆን ያለበት መጀመርያ የእሳት አደጋ ከመድረሱ በፊት አስፈለጊዉን የመከላከያ መዋቅሮችን መዘርጋት ነው።

ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ደግሞ መንግሥት ብቃት ያላቻው ምሁራን ፖሊሲ እንድያረቁና ምልአተ ሕዝቡን እንድያስተምሩ መፍቀድ አለበት። ምሁር ሲባል ግን ካድሬ ሳይሆን ነጻና ገለልተኛ የሆነ ምሁር ለሃገር የሚቀረቀርና ዘለቄታ ያለው ፖሊሲ ማርቀቅ የሚችል ለማለት ነው። ብቃት ያለው ምሁር ሲባል ደግሞ አንደኛ

ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ያለው ብቻ ሳይሆን ጠለቅ ባለ መንገድ ነገሮችን መመርመር የሚችልና ማሕበራዊ ጉዳዮችን ከአግባብነት ያላቸው ስነ-ሀሳቦች ማገናዘብ የሚችል ማለት ነው። ምሁሩ በተክኒካዊ ወይም ሞያዊ ስልጠና የተካነ ብቻ ሳይሆን መጠነ ሰፊ ፍልስፍናዊ አመለካከትና ራእይ ያለው ሆኖ ሁለገብ ችሎታዎችን ያካበተ መሆንም አለበት።

ለምሳሌ በምዕራፍ አንድ የጠቀስኳቸውን የአዲስ አበባ የማሕበራዊ ደኅንነት ድሕረ-ምረቃ ተማሪዎች ባቀረብዋቸው ጥናቶች አግባብነት ያለቸው ተመራማሪዎች እንደ ዱርካይም እና ቪበር ወይም ሚልስ አይጠቅሷቸውም። በምዕራፍ ሁለት በዩኒሰፍ ስለ ማሕበራዊ ግልጋሎት በኢትዮጵያ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ በተመሳሳይ መልኩ የስነ-ሐሳብ ግድፈት ይታይበታል፣ ስለሆነም ጥናቱ ማሕበራዊ ጉዳዮችን በገረፍታ ወይም በመቆንጨብ ነው የሚተነትናቸው። እንዲህ ዓይነት ጥናቶች በመጠኑ ጥቅም ቢኖራቸውም ቅሉ፡ ጠለቅ ባለ መንገድ ማሕበራዊ ችግሮችን ለመገንዘብና መፍትሔዎችን ለማቅረብ ግን አይረዱንም።

ምዕራፍ ሦስት፣ 'እርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ'፣ የተባበሩት መንግሥታት የሚለንየም ግብ ነው የሚያንጸባርቀው። ኢትዮጵያም የተባበሩት መንግሥታት አባል ስለሆነች አንዳንድ ግቦችን በግብር መተርጎም ግዴታ አለባት። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ የእርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የግድ የሚለንየም ግብ ቀጥተኛ ቅጂ መሆን የለበትም፣ ከኢትዮጵያ ተጫባጭና ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣምና ከተተገበረም በኋላ ስኬታማ እንደሚሆን ዋስትና የሚሰጥ ፖሊሲ ነው መርቀቅ ያለበት። በተጨማሪም አስቀድሜ እንደጠቀስኩት የጊዜ ገደቡ ትርጉመቢስ ነው። በ2015 ዓ.ም. ሁሉም ፕሮጀክቶች ግባቸውን መምታት አለባቸው ማለት ከታዳጊ አገሮች ተጫባጭ ሁኔታ ጋር የማይሄድ ፖሊሲ ነው። ታዳጊ አገሮች እንደየአቅማቸውና እንደየችሎታቸው ነው መጓዝ ያለባቸው እንጂ አንድ ዓይነት ጓንቲ ተጠቅመው ልማትን ማጣደፍ አለባቸው ማለት እጅግ በጣም የተሳሳተ አማለካከት ነው።

በምዕራፍ አራት እንዳየነው ጥናቱ ያቀረቡልን ግለሰቦች ስለ 'እርጅና እና ድህነት በኢትዮጵያ' ጠቃሚና በስታቲስቲክስ የተደገፈ ትንተና ቢያደርግም፣ ጥናቱ በመጠን እንጂ በዓይነት የምርመራ ስልት ላይ የተመረኰዘ አይደለም። በዚህም ላይ የጥናቱ አቅራቢዎች የመንግሥት ሠራተኞች ስለሆኑ ከመንግሥት ፖሊሲ ውጭ የራሳቸውን አቋም ይዘው በጉባኤው መቅረብ አይችሉም። ስለሆነም የዱርካይም ጥያቄ 'ግለሰቦች ከድንጋጌ ነጻ ወጥተው በሕብረተሰባቸው ወስጥ ሐላፊነትን መሸከም ይችላሉ ወይ?' ለሚለው ጥያቄ መልሱ 'አይችሉም' ነው።

በምዕራፍ አምስትም እንደዚሁ የቡና ጊዜ ስትራተጂ ለምን ስኬታማ እንዳልሆነ አይተናል። ፕሮግራሙ ከወጣ በኋላ ሲተገበር አወያዮቹ አስፈላጊውን ስልጠና ሳይሰጣቸው ነበር የቡና ጊዜው የተጀመረው። ይህ የሚያሳየው የዝግጁነት ጉድለት ብቻ ሳይሆን ቅድመ-ጥናት ሳይካሄድ በመቅረቱም ጭምር ነው። ቤት ሲሰራ ለህንጻው የሚያስፈልጉ ቁሳዊ ነገሮችና መሳርያዎች ብቻ ሳይሆኑ የስነ-ህንጻ በላሙያዎችም ጭምር ነው የሚያስፈልጉት።

ለነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸውን ማሕበራዊ ችግሮችን ለማጥናትና መፍትሔ ለማበጀት መጀምርያ መደረግ ያለበት ሰፋ ባለ መልኩ ማሕበራዊ ስነ-ሐሳቦችን ማጥናት ነው። ነገር ግን እነዚህ ስነ-ሐሳቦች መንገድ ለመቀየስ ይረዱናል እንጂ ቅድም እንደተጠቀሰው ያልተጠበቀ የታሪክ ክስተት ሊፈጠር ስለሚችል አማራጮችን መፈለግ የግዴታ ነው የሚሆነው። ምሳሌ ለምሰጠት ያህል ካርል ማርክስና ማክስ ቬበር ከወሰድን ማርክስ በሚያስደንቅ መንገድ የካፒታሊዝም ባሕርይ ከመተንተን አልፎ አቅጣጫው ሳይቀር - ማለትም አሁን የተከሰተው የዓለም አቀፍ የኮርፖረሽን ወረራ (globalization) - በመተንበይ አቅርቦታል። ሆኖም ግን 'ከካፒታሊዝም ወደ ሾሻሊዝም ሽግግር' የሚለውን የማርክስ አብዮታዊ ተስፋ እንደታሰበውና እንደተጠበቀው አልተሳካም። ማርክስ ያላያቸውን ሁለት ነገሮች 1) ካፒታሊዝም በውስጡ ቅራኔ የሚንኮታኮት ስርዓት ከመሆን ይልቅ በተቃራኒው በየጊዜው ማሻሻያዎችን እያደረገ ቀጣይነትን የሚየሳይ (resilient) ስርዓት ለመሆኑ፣ 2) በብዙ ካፒታሊስት አገሮች የተከሰተውን የዴሞክራሲ ስርዓት ልዩ ልዩ የሕብረተሰቦችን አባላት በመጠኑም ቢሆን ፍላጎታቸውን የሚያስተናግድ ስለሆነ።

ማክስ ቬበርም ስለ ሕጋዊነትና በምርምር የተደረሰበት ጥናት እንዲሁም የሲቪል አስተዳደር (bureaucracy) በሰፊውና አሳማኝ በሆነ መንገድ አቅርቦልን ከሄደ በኋላ የኅብረሰባዊ ትምህርት ሊቃውንት አስካሁን ድረስ ቬበርን በመንተራስ ነው ጥናታቸውን የሚጀምሩት። ነገር ግን ቬበር ማየት ያልቻለው (ማየትም አይችልም) በዓለም አቀፍ ደረጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተው ነገር ቢኖር አዲሱ የኢንተርነት መገናኛ ነው። ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ኮርፖረሽኖች ለምሳሌ አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ንብረተ-ተቋማቸውን የሚያስተዳድሩት በቢሮ አማካኝነት ሳይሆን በኢንተርነት ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ኮርፖረሽን እንደ አማዞን እና ኢ-በይ የመሳሰሉት ከናካቴው ቢሮውን ትተው በጥቂት ስውር በሆኑት የኢንተርነት ባለሙያዎች አማካኝነት በዓለም ዙርያ ንግድ ያካሂዳሉ።

አንድ መንግሥት ፖሊሲ ሲያረቅ ታድያ ሰፋ ያለ አመለካከት ያላቸውና ነገሮችን ማገላበጥ የሚችሉ ገለልተኛ ምሁራንና በለሙያዎች ካልያዘ ምንጊዜም ጥፋትና ውድቀት ይኖራል። መፍትሔው ፖለቲካዊ ነው፣ ለፖለቲካ ደግሞ መልሱ ፖለቲካ ነው። ለሁሉም ማሕበራዊ ችግሮች መፍትሔ ከተፈለገ ደግሞ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ የጥናትና ምርምር ዘዴ መጠቀሙ ይበጃል።

## ዋቢ ጽሑፎች


1. August Comte, *Introduction to Positive Philosophy*
2. Emile Durkheim, *The Division of Labor in Society*
3. Karl Marx, *Capital; Capital: Critical Analysis of Capitalist Production*
4. Max Weber, *Protestant Ethics and The Spirit of Capitalism*
5. Antonio Gramsci, *Prison Notebooks*
6. C. Right Mills, *White Collar; The Power Elite; The Sociological Imagination*
7. ገላውዴዎስ አርአያ፣ መንከባከብና ማስወገድ ያሉብን ባህሎች 2000/2008

8. Ghelawdewos Araia, Ethiopia: Democracy, Devolution of Power, and The Developmental State, 2013
9. Addis Ababa University Graduate School of Social Work, *Social Policy Reader*, Vol. 3, 2008
10. Ethiopian Statistical Abstract, 2001
11. World Health Organization Report 2005
12. Kelly Bunkers and Douglas Webb, *Social Welfare Services in Ethiopia: Typology and Costs*, UNICEF Ethiopia, November 2011
13. Stephen Devereux and Bruce Guenther, *Agriculture and Social Protection in Ethiopia*, FAC Working Ppaer no. SP03, January 2009
14. Assefa Baleher and Frehiwet Yirsaw, *Regional Workshop on Ageing and Poverty*, Dar es Salam, October 2003
15. Anteneh Mekuria Tesfaye, *Piggybacking the Traditional Coffee Ceremony as a Participatory Communications Strategy to Resolve Social Problems: an Assessment of Practices in Addis Ababa, Ethiopia, Bahir Dar University*
16. Commonwealth of Australia, *Ethiopian Community Profile*, August 2006

**All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA) 2014** **Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted via [dr.garaia@africanidea.org](mailto:dr.garaia@africanidea.org)**